# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 283 ሰኔ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የኮሪደር ልማቱ ተጨማሪ ትሩፋት

ቃልኪዳን አሳዬ

**ዜና ሐተታ**

አካባቢው እጅጉን ተቀይሯል። አላፊ አግዳሚውም በየቀኑ እየመጣ ያለውን ለውጥ በአግራሞት መመልከት ከጀመረ ሰንብቷል። እግረኛው ደከም ሲለውም በየመንገድ ዳሩ በተሰናዱ መቀመጫዎች ላይ አረፍ በማለት መንፈሱን ያድሳል። የአካባቢው የማታም ሆነ የቀኑ ድባብ ለየት ያለ ሆኗል።

ለዜጎች የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠትና የአዲስ አበባ ከተማን የአፍሪካ መዲናነት ለማጽናት እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች መካከል በተመረጡ የከተማዋ አካባቢዎች እየተከናወነ ያለው የኮሪደር ልማት አንዱ ነው።

በዚህም ልማቱ ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ

የኮሪደር ልማቱ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ አክሊሉ አበበ



አቶ ፍቅሩ ሀብተማርያም






# በመስኖ ስንዴ ከ106 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተገኝቷል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- በ2016 የምርት ዘመን በመስኖ ስንዴ ከ106 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መገኘቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ኢሳያስ ለማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ በ2016 የምርት

በመስኖ ስንዴ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “ኢትዮጵያ በሚገባት ልክ እንዳልተገኘች የሚያስብ ዜጋ ሁሉ በበጎ ፍቃድ ሥራዎች ላይ ሊሳተፍ ይገባዋል”

-አቶ ተመስገን ጥሩነህ ም/ጠቅላይ ሚኒስትር

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በሚገባት ልክ እንዳልተገኘች የሚያስብ ዜጋ ሁሉ በበጎ ፍቃድ ሥራዎች ላይ ሊሳተፍ ይገባዋል ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ

“ኢትዮጵያ በሚገባት ልክ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አረንጓዴ አሻራ የሱማሌ ክልል በረሃማ አካባቢዎችን ወደ አረንጓዴነት እየመለሰ ነው

## -በዓመቱ ከታቀደው የችግኝ ተከላ ፕሮግራም እስካሁን 80 በመቶ ያህሉ ተሳክቷል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብር የሱማሌ ክልል በረሃማ አካባቢዎችን ወደ አረንጓዴነት እየመለሰ መሆኑ ተገለጸ፡፡ በክልሉ በ2016 ዓ.ም ከታቀደው የችግኝ ተከላ ፕሮግራም እስካሁን 80 በመቶ ያህሉ እንደተሳካም ተጠቁሟል፡፡

የሱማሌ ክልል አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር አስተባባሪ አቶ መሐመድ ቡሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በክልሉ እስካሁን ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ይገኛል፡፡ በርካቶች ተሳትፎ አድርገው የሥራ ዕድል ያገኙበት ሲሆን፤ ሰፊው የኅብረተሰብ ክፍል ባከናወነው ሥራም የክልሉ በርሃማ አካባቢዎች ወደ አረንጓዴነት እየተቀየሩ ይገኛሉ፡፡



አስተባባሪው እንዳሉት፤ አካባቢው በረሃማ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የአየር ንብረት ለውጡ፤ የአፈር መሸርሸርና መሰል ችግሮች የነበሩበት ነው፡፡ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከተጀመረ ወዲህ በርካታ ችግኞች ተተክለዋል፡፡ በዚህም

አረንጓዴ አሻራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






አቶ እንዳሻው ጣሰው

# በክልሉ በጸጥታ ምክንያት የተቋረጠውን የሌሊት የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ለማስጀመር እየተሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በጸጥታ ምክንያት የተቋረጠውን ወደ አዲስ አበባ የሚደረግ የሌሊት የትራንስፖርት አገልግሎት ለማስጀመር እየተሠራ ነው ሲሉ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው ተናግረዋል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ወደ አዲስ አበባ የሚወስዱና ከአዲስ አበባ ወደ ክልሉ በሚያስገቡ መንገዶች ላይ የሚታዩ የጸጥታ ችግሮችን በመፍታት መኪናዎች በቀን የጊዜ ሰሌዳ በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ ተደርጓል፤ ከአዲስ አበባ ወደ ክልሉ፤ ከክልሉም ወደ አዲስ አበባ የተቋረጠውን በማታ የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴን ለማስጀመር ጠንካራ ሥራ እየተሠራ ነው።

ከአዲስ አበባ ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሚያስገቡ መንገዶች ማለት በወሊሶ፣ በቡታጅራ፣ በቀለበት መንገድ በዝዋይ ወደ ክልሉ በሚያስገቡና እና ከክልሉ ወደ አዲስ አበባ በሚያስወጡ መስመሮች ላይ ሸኔ የሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች በመሆናቸው ችግሮች ነበሩ ብለዋል።

ክልሉ ከተዋቀረ በኋላ የጥፋት ቡድኑ በተሽከርካሪዎችና በተጓዦች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማስቀረት ከሀገር መከላከያ ሠራዊትና ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ጋር የቅንጅት ሥራ ተሠርቷል ያሉት አቶ እንዳሻው፤ በተሠራውም ሥራ ተሽከርካሪዎች በቀን ያለምንም የጸጥታ ስጋት መንቀሳቀስ ችለዋል ብለዋል።

አልፎ አልፎ የሚሸሽግ የጥፋት ኃይል ሰዓት እየጠበቀ መኪና የማቃጠል ድርጊት ይፈፅማል፤ በተለይ በቡታጅራ በኩል ከሌመን ወደ ክልሉ በሚያስገባው መስመር ላይ ድርጊቱ በቅርብ ጊዜ ተፈፅሟል ያሉት ርዕሰ መስተዳደሩ፤ አልፎ አልፎ የጥፋት ኃይል ሲሸሽ የሚያደርሳቸውን ችግሮች ለመፍታት ጠንካራ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ክልሉ ወደ አዲስ አበባ የሚያስወጡና የሚያስገቡ መንገዶችን ከስጋት ቀጣና ነፃ በማድረግ መኪናዎች በማታ የጊዜ ሰሌዳ እንደፈለጉ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ በትኩረት እየሠራ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

አቶ እንዳሻው አያይዘውም፤ "በክልሉ ውስጥ በምሥራቅ ጉራጌ ምሥራቅ መስቃንና በማረቆ አካባቢዎች፣ በወልቂጤ አካባቢ በቀቤናና በጉራጌ ወንድማማቾች የተፈጠሩ ግጭቶች ነበሩ፤ የተፈጠሩት ግጭቶች ሕዝብ ለሕዝብ አልነበሩም፤ የጥቂት ግለሰቦች ፍላጎቶች ናቸው። የተፈጠሩ ችግሮችን በአካባቢ ሽማግሌዎች በእርቅ ከስር ከመሠረታቸው እንዲፈቱ ተደርጓል፤ አሁን ክልሉ ሙሉ ለሙሉ ሰላም ነው፤ ሰዎች በሰላም አምሽተው የሚሰሩበት፣ በሰላም ወጥተው የሚገቡበት ነው" ሲሉም ገልጸዋል።

በክልሉ ያለውን ሰላማዊ እንቅስቃሴ አጠናክሮ ለማስቀጠል ማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት የማደራጀት፣ ማህበረሰቡን የማስተማር፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከባለሀብቶች ፣ ከወጣቶች፣ ከእናቶችና በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ከተደራጁ ዜጎች ጋር ቀጣይነት ያለው ውይይት ማድረግና ወደ ወንጀል የተቀየሩ ጉዳዮችን በሕግና በሥርዓት እንዲዳኙ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉም አመላክተዋል።

# በክልሉ በመኸር እርሻ ከ10 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በሰብል ዘር ለመሸፈን እየተሠራ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ቦረና፡- በኦሮሚያ ክልል በመኸር እርሻ ከ10 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ በዘር ለመሸፈን ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ። እስካሁን በተሠራ የግብርና ሥራ ሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰብል ዘር መሸፈኑ ተገልጿል።

የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በምሥራቅ ቦረና ዞን በመገኘት የግብርና ልማት እንቅስቃሴን ጎብኝተዋል።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በጉብኝቱ ወቅቱ እንደገለጹት፤ በክልሉ በመኸር እርሻ 10 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በሰብል ዘር ለመሸፈን ታቅዷል።



አቶ ጌቱ ገመቹ

አጠቃላይ በመኸር ወቅት በሰብል ዘር ከሚሸፈነው መሬት ውስጥ ስምንት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት የሚሆነው በኩታ ገጠም እርሻ የሚዘራ ነው ያሉት አቶ ጌቱ፤ እስካሁን ዘጠኝ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ማረስ ተችሏል ብለዋል።

በክልሉ ያለውን አቅም አሟጦ ለመጠቀም ቀድሞ ለግብርና የሚያስፈልግ ግብዓት ማሟላት ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራቱንም ነው አቶ ጌቱ የጠቆሙት።


እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ በተለይ በቆላማና በድርቅ ሲጎዱ የነበሩ አካባቢዎች ላይ በተለየ ሁኔታ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል።

በክልሉ የተሻለ የዝናብ ስርጭት አለ ያሉት አቶ ጌቱ፤ በክልሉ በበልግ እርሻ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን ጠቅሰዋል፡፡ ለመኸር እርሻ ውጤታማነትም በቂ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል።

ከዚህም 28 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል ያሉት አቶ ጌቱ፤ የዘንድሮ ዝናብ ቀደም ብሎ መጀመሩ የበልግ እርሻ ከታቀደው በላይ እንዲሳካ ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል።

የምሥራቅ ቦረና ዞን ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ መስቀሉ ቱሉ በበኩላቸው፤ በዞኑ በበልግ እርሻ 141 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በዘር መሸፈኑን ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት ቦረና የሚታወቀው በእንስሳት እርባታ ነው ያሉት አቶ መስቀሉ፤ አሁን ሙሉ በሙሉ የተጠናከረ እርሻ እየታረሰ እንደሚገኝ ገልጸዋል።



# ማዕከሉ ለተረጂዎቹ ማቆያ ለሚያስገነባው ሕንፃ ኅብረተሰቡ ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቀረበ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በጅማ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ አጋዥ የሌላቸው አረጋውያንና ሕፃናት የሚረዳው ሰው ለሰው የሕፃናትና አረጋውያን መርጃ ማዕከል ለሕንፃ መገንቢያ የሚሆን የእርዳታ ጥሪ አቀረበ።

የማዕከሉ መስራች ወይዘሮ ዘመናይ አስፋው እንዳሉት፤ ማዕከሉ አንድ የስድስት ወር ጨቅላ እና ሦስት አረጋውያንን በመንከባከብ ከሰባ ዓመታት በፊት ሥራ መጀመሩን ይገልጻሉ።

ይህ የበጎ አድራጎት ድርጅት በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በራሳቸው ወጪ መንከባከብ የጀመሩት ወይዘሮዋ፤ አሁን ላይ 500 አረጋውያን አንድ መቶ የአእምሮ ሕሙማን እንዲሁም 126 ጨቅላ ሕፃናትን በመንከባከብ ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

በመሆኑም ማዕከሉ የመኖሪያ ሕንፃ እና በጀት ስለ ሌለው ለችግር እየተጋለጠ ይገኛል፤ሕፃናት የሚጠጡት ወተት፣ምግብ እንዲሁም አልባሳት ያስፈልጋቸዋል፤ ይህ ደግሞ ለመኅብኘት ከሚመጡት በጎ አድራጊዎች እና የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ድጋፍ የሚገኝ ነው ብለዋል።

ስለሆነም የጅማ ከተማ አስተዳደር አምስት ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ለማዕከሉ የሰጠ ሲሆን፤ሕንፃውን ለመሥራት 47 ሚሊዮን ብር ያስፈልጋል ብለዋል።


ማዕከሉ ምንም በጀት ባይኖረውም ለመኅብኘት በሚመጡ በጎ ሰዎች ሲደገፍ እንደቆየም ጠቁመዋል።

የጅማ ከተማ ሴቶች እና ሕፃናት ጉዳይ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሪት ኢክራም አብዱ ዝግጅቱ ላይ የተገኙ ሲሆን፤ጅማ ነባር ከተማ ከመሆንዋ ጋር ተያይዞ ማህበራዊ ኃላፊነት ለመወጣት ከማዕከሉ ጋር አብረን እንሠራለን ብለዋል። ለሕንፃ ማሰሪያውም ቢሆን መንግሥት የራሱን ድጋፍ እንደሚያበረክት ቃል ገብተዋል።



ማዕከሉ ሁለቱም አንጋፋ አርቲስቶች፤ አርቲስት ፍቅርተ ደሳለኝ እና አርቲስት ሰለሞን ተካልኝ የበጎ አድራጎት አምባሳደር አድርጓቸዋል።

ማዕከሉ እንዲገነባ ሁሉም ሰው የአቅሙን እርዳታ እንዲያደርግ ጥሪ ያቀረቡት መስራቿ፤ለቀጣይ ጅማ ከተማ እና በአዲስ አበባ ላይ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀ ግብር እንደሚካሄድ ጠቁመዋል።



አቶ ገመቹ ጉርሜሳ

# በዞኑ ሰላም በመስፈኑ ኅብረተሰቡ ፊቱን ሙሉ ለሙሉ ወደልማት መልሷል

በኃይሉ አበራ

ደምቢዶሎ፡- በኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ ዞን ሰላም በመስፈኑ ኅብረተሰቡ ፊቱን ሙሉ ለሙሉ ወደልማት መልሷል ሲሉ ዋና አስተዳዳሪው አቶ ገመቹ ጉርሜሳ ተናገሩ።

አቶ ገመቹ ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ የለውጥ እንቅስቃሴ በተደረገበት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የቄለም ወለጋ ዞን ፈታኝ የሰላምና የልማት ችግር ውስጥ ቆይቷል። ችግሮቹን በመቅረፍ አሁን ላይ የተለያዩ የልማት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

ሰላምን ከሚፈልገው ኅብረተሰብ ጎን በፌዴራል የሰላም አደረጃጀት፣ በኦሮሚያ ክልልና በዞኑ ሚሊሻም አማካኝነት አሁን ላይ በተከናወኑ የልማት ሥራዎች ውጤት እየተገኘ መሆኑን አንስተዋል።

በዞኑ ከ2008 እስከ 2016 ዓ.ም ድረስ የቆየውን የሰላም እጦትና ፈታኝ ሁኔታ ታሪክ ለማድረግ በግብርናው፣ በመሠረተ ልማትና በኢንቨስትመንቱ የተለያዩ ሥራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውን የዞኑ አስተዳዳሪ አስረድተዋል።

በዞኑ ለእርሻ ልማት ሊውል የሚችል 109 ሺህ 90 በላይ ሔክታር መሬት ላይ 467 ሺህ ሔክታር በላይ የቡና ልማት እንዳለ ጠቁመው፤ በዚህ ዓመትም 367 ሺህ ሄክታር ተጨማሪ መሬት በማዘጋጀት የግብርና ሥራውን ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

በዞኑ ከ150 ሺህ ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ መቅረቡንና 50 በመቶ ለአርሶ አደሮች መሰራጨቱን አስታውቀዋል። በተጨማሪም ከአራት ሺህ በላይ ኩንታል ምርጥ ዘር መሰራጨቱን ጠቁመዋል።

የቡና ምርታማነትን ለማሳደግ በ2015/16 የምርት ዘመን 197 ሚሊዮን ችግኝ መተከሉን አስታውሰው፤ በመንግሥትና በሕዝብ በተቋቋሙ የችግኝ ጣቢያዎች አማካኝነት ከባለፈው ዓመት ጀምሮ 378 ሚሊዮን የቡና ችግኞች በዞኑ እየተተከሉ መሆኑን አስታውቀዋል።

የከተማና የገጠር ልማት ሥራዎች በማከናወን የዞኑን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን አንስተው፤ ዞኑ ካለው የውሃ ሀብትና ለም መሬት አንጻር በቀጣይም የተጠናከረ ሥራ ማከናወን ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ከግብርናው በተጨማሪ በእንስሳት ሀብት፣ በወተት፣ በዶሮ እርባታና በተለያዩ ምርቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

በዞኑ ሲንቀሳቀስ የነበረው ፀረ-ሰላም ኃይል ወደ ድንበር ተበታትኖ ይገኛል ያሉት አስተዳዳሪው፤ በሌላ በኩል በሰላማዊ መንገድ ለመንቀሳቀስ እጃቸውን ለመንግሥት የሰጡ ታጣቂዎች መኖራቸውንም ጠቁመዋል። አሁን ላይ በዞኑ ሰላም በመስፈኑ የፌዴራል የሰላም አደረጃጀት፣ ከክልሉና ከዞኑ የጸጥታ አካላት ጋር በትብብር የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

የቄለም ወለጋ ዞን በኦሮሚያ ከሚገኙ ዞኖች አንዱ ሲሆን፤ 12 ወረዳዎችና 279 ቀበሌዎች አሉት።

# የተሻሻለው የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ ማሻሻያ ዝቅተኛ የማህበረሰብ ክፍሎችን አይነካም

ሔርሞን ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ መልክ የተሻሻለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አከፋፈል ዝቅተኛ የማህበረሰብ ክፍሎች እና መሠረታዊ ፍጆታዎችን እንደማያካትት ተገለጸ።

የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ኢዮብ ተካልኝ(ዶ/ር) በተሻሻለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ዙሪያ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው በሰጡት ማብራሪያ፤ መሠረታዊ ፍጆታ በተለይ ለዝቅተኛ የማህበረሰብ ክፍሎች አስፈላጊ የሆኑ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣የውሃ ፍጆታ የመሳሰሉ እና የምግብ (ዳቦ እና እንጀራ) ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ አይከፈልም ብለዋል።

የወጣው የአዋጅ ማሻሻያ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸውን እንዳይነካ በጥንቃቄ መሠራቱን የገለጹት ዶክተር ኢዮብ፤ የገንዘብ ሚኒስቴር ከተወሰነ ልኬት በታች የሚጠቀሙትን የውሃ እና የኤሌክትሪክ ፍጆታዎች ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ማደረጉን ጠቅሰዋል።

ሆኖም መንግሥት ኤምባሲዎችን እና ትልልቅ ሆቴሎችን የሚደጉምበት ምንም ዓይነት ምክንያት ባለመኖሩ፤ በፊት የነበረውን ኢ ፍትሃዊ አሠራር ለማስተካከል ተብሎ አዋጁ እንዲስተካከል መታመኑን አብራርተዋል።



ኢዮብ ተካልኝ(ዶ/ር)

የተጨማሪ እሴት ታክስ በሥራ ላይ ከዋለ ወዲህ በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ላይ የተደረጉ ለውጦችን ያገናዘበ ሕግ ለፋይናንስ አገልግሎት የተሰጠው ከታክስ ነጻ የመሆን መብት፤ ተቋሙን ሳይሆን የአገልግሎቱን ባህሪ እንደሚመለከትም አብራርተዋል።

ይህም ለፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ የተሰጠው ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የመሆን መብት ተፈጻሚ የሚሆነው፤ ተቋማቱ ብድር ከመስጠት፣ ከመሰብሰብ እና ከተቀማጭ ገንዘብ ጋር በተያያዘ ለሚሠሩት ሥራ እንደሆነ ጠቅሰዋል። በተጨማሪም አክሲዮን፤ ቦንድ እና ሌሎች የዋስትና ሰነዶችን ከመገበያየት፤ የኢንቨስትመንት ፈንድ ከማስተዳደር እና የጡረታ ፈንድ ከማቋቋም ጋር የተያያዘው ብቻ ከታክስ ነፃ እንዲሆን ተደርጓል ብለዋል።

በተወሰነ ክፍያ ማለትም የኮሚሽን እና የአገልግሎት ክፍያ የሚሰጡትን አገልግሎቶች እንዳይጨምር ማድረግ፤ በሸሪአ ሕግ መሠረት ከሚሰጡ የፋይናንስ አገልግሎቶች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጥ ኩባንያ ለወኪሎቹ የሚሰጠው ቅናሽ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ታክሱን በሙሉ ዋጋ ላይ እንዲሰበስብ፤ የሮሚንግ ስልክ አገልግሎት ታክሱ የሚከፈልበት በኢትዮጵያ እንዲሆን መደረጉን አብራርተዋል።

ከ70 ሚሊዮን ብር በታች ዓመታዊ ግብይት ያላቸው በየሦስት ወሩ እንዲከፍሉ ሲደረግ የነበረው አሠራር መቅረቱን እና ታክሱን የመክፈያ ጊዜ በየ30 ቀን እንዲሆን ተደርጓልም ብለዋል።

# ሕጋዊ የሥነ ልክ ረቂቅ አዋጁ በነጋዴውና በሸማቹ መካከል ያለውን አለመተማመን በመከላከል የንግድ ማጭበርበርን ያስቀራል

መዓዛ ማሞ



አዲስ አበባ፡- ሕጋዊ የሥነ ልክ ረቂቅ አዋጁ በነጋዴውና በሸማቹ ማህበረሰብ ያለውን አለመተማመን በመከላከል የንግድ ማጭበርበርን የሚያስቀር መሆኑን የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጠቆመ፡፡ ሕጋዊ የሥነ ልክ ረቂቅ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይፋዊ የሕዝብ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ አቶ አስቻለው አለምዬ እንዳሉት፤ አዋጁ የንግድ ሥርዓቱን ታማኝነት ለማረጋገጥ ፣ በነጋዴውና በሸማቹ ማህበረሰብ ዘንድ መተማመን በመፍጠር እና ሕጋዊ የንግድ ሥርዓት ለመፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

አዋጁ ዓለም አቀፍ የንግድ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን ተናግረው፤ በረቂቅ አዋጁ ላይ በየደረጃው ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይቶች በመደረጋቸው ትልቅ ግብዓት መገኘቱን ገልጸዋል፡፡

በይፋዊ የውይይት መድረኩ ረቂቅ አዋጁን ያቀረቡት በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሕጋዊ ሥነ ልክ እና ቴክኒክ ደንብ ማስተባበሪያ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌታቸው ጥሩነህ እንዳሉት፤ የአዋጁ ዓላማ ለንግድ ልውውጥ፣ ለሰውና ለእንስሳት ጤናና ደህንነት፣ እንዲሁም ለአካባቢ ጥበቃ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመለኪያ መሣሪያዎችንና ልኬቶችን ወጥነት እና ትክክለኛነት ማረጋገጥ ነው::

አዋጁ የታሸጉ ምርቶችን የተጣራ መጠን ትክክለኛነት በማረጋገጥ የኅብረተሰቡን እና የእንስሳት ጤናና የአካባቢ ደህንነት እንዲጠበቅ እንደሚያደርግ ተናግረው፤ ሸማቹ ለከፈለው ዋጋ ተመጣጣኝ ምርትና አገልግሎት እንዲያገኝ፣ ፍትሐዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍን እና ከዓለም አቀፍ የንግድ ግንኙነት ጋር የተጣጣመ ሥርዓት እንዲኖር ምቹ መደላድል የማድረግ ዓላማ እንዳለው ጠቁመዋል፡፡

ሕጋዊ የሥነ ልክ በቁጥጥሩ ዘርፍ በ1965 ዓ.ም ጥቂት ገጾች ብቻ ያሉት ደንብ ወጥቶለት እስከ አሁን ሲሠራበት እንደነበረ ተናግረው፤ ደንቡ ቴክኖሎጂውን ያላገናዘበ፣ የመለኪያ መሳሪያዎችና ሌሎች ጉዳዮች በሚገባ ያልተገለጹበት ፣ ቅጣቶች ያልተደነገጉበት እና ዝርዝር የሥነ ልክ ጉዳዮች ያልተካተቱበት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

አዋጁ ሲጸድቅ አሁን በሥራ ላይ ያለውን ደንብ በመተካትና ያሉትን ክፍተቶች በመሙላት ሥራዎችን ሁሉ አቀፍ በሆነ መንገድ ለመሥራት እንደሚያስችል ተናግረው፤ ለኢትዮጵያ አዲስ እና ፈር ቀዳጅ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በአዋጁ ክልከላዎች እና እንደ ግዴታ የተቀመጡ ጉዳዮች መኖራቸውን የተናገሩት አቶ ጌታቸው፤ ልኬቶችንና የመለኪያ መሳሪያዎችን እና የታሸጉ ምርቶችን በሚጠቀሙ፣በሚያመርቱ፣ በሚያስገቡ እና በሚልኩ ላይ ክልከላዎች እና ግዴታዎችን ማካተቱን አብራርተዋል፡፡

ከደረጃ በታች የሆነ የልኬት መሳሪያ፣የተዛባ መሳሪያ፣የጥራት ማረጋገጥ ያልተደረገባቸው፤ እንዲሁም የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው የልኬት መሳሪያዎች ክልከላዎች መደረጉንም ጠቁመዋል፡፡ ክልከላዎቹ ከአስተዳደራዊ እርምጃ ጀምሮ ወንጀል ነክ ሆነው ፍርድ ቤት ሊያስወስዱ የሚችሉ መሆናቸውንም አክለው ገልጸዋል፡፡

ከተሳታፊ ባለድርሻ አካላት በረቂቅ አዋጁ ላይ ነጋዴው ማህበረሰብ የሚጠቀምበትን ሚዛን ዲጂታል እንዲሆን የሚያስገድድ ሕግ ቢካተትበት፣ቅጣቶች በግልጽ ቢቀመጡ እንዲሁም የሥነ ልኬት መሳሪያዎችን የማያስፈትሹ ነጋዴዎች ላይ ቅጣት የሚጥል አንቀጽ ቢካተትበት የሚል ሃሳብ ቀርቧል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ገብረመስቀል ጫላ በምላሻቸው የተሰጡ አስተያየቶች ገንቢ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በረቂቅ አዋጁ እንደሚካተቱ ጠቁመዋል፡፡

የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አሻ ያህያ በሰጡት ማጠቃለያ፤ የተነሱ ሃሳቦች ለረቂቅ አዋጁ እንደ ግብዓት እንደሚሆኑ ጠቁመው፤ ጥያቄዎች እና ሃሳቦች ካሉ በጽሑፍ በሁለት ቀናት ውስጥ መላክ እንደሚቻል አመላክተዋል፡፡

# የ6ኛ ዙር ጠቅላላ ምርጫ ቀሪና ድጋሚ ምርጫ በመጪው እሁድ ይካሄዳል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፦ በጸጥታና ሌሎች ችግሮች ምክንያት የ6ኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ ባልተከናወነባቸው ሱማሌ ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ፣ ቤኒሻንጉልና አፋር ክልሎች ሰኔ 16/2016 እንደሚከናወን ተገለጸ።

የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን የ6ኛውን የድጋሚና ቀሪ ምርጫ የዝግጅት ሥራዎችና አጠቃላይ የሥራ አፈጻጸም ተመልክቷል።

በአራቱ ክልሎች ምርጫ ባልተካሄደባቸው 29 የምርጫ ክልሎች በሚካሄደው የድጋሚና ቀሪ ምርጫ ከ1258 በላይ የምርጫ ጣቢያዎች መዘጋጀታቸውን የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ሜላተወርቅ ኃይሉ ገልጸዋል።

የመራጮች ምዝገባ ሰነድ በጠፋባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ መከናወኑንና ከ 1 ሚሊዮን በላይ መራጮች እንደሚሳተፉ ሰብሳቢዋ ገልጸዋል።

በምርጫው የምርጫ አካባቢያቸውን በሕዝብ ተወካዮችና በክልል ምክር ቤት የሚወክሉ 380 ዕጩዎች መመዝገባቸውንና 76ቱ ሴቶች መሆናቸውን ቦርዱ አስታውቋል።

ምርጫው የሚካሄድባቸው ገለልተኛ ቦታዎች መመረጣቸውንና 6380 የምርጫ አስፈጻሚዎች እንደሚሳተፉ ተገልጿል።

ምርጫውን ነፃና ተአማኒ ለማድረግ የምርጫ ታዛቢዎች በበቂ ሁኔታ መመደባቸውና የቅሬታ ማቅረቢያ መንገዶች መዘጋጀታቸውም ተጠቁሟል።



ወ/ሮ ሜላተወርቅ ኃይሉ

# አረንጓዴ አሻራ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በርካታ የተጎዱ መሬቶችን ማዳን ተችሏል፡፡

ለግብርና የሚውሉ ችግኞችን በማብዛት ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ያሉት አቶ መሐመድ፤ የተጀመረውን የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በማጠናከር ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተያያዙ በርካታ ችግሮች በቅርብ እንደሚፈቱ ገልጸዋል፡፡

በክልሉ በርካታ ችግኞች በመተከላቸው በተለይም የተጎዱ አካባቢዎችና ከተሞች ላይ መሬቱ እየለማ እንዳለ ጠቅሰው፤ ይህም በርሃማ አካባቢዎችን ወደ አረንጓዴነት እየመለሰ እንዳለ ተናግረዋል፡፡ መርሀ ግብሩም በርሃማነትን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያለው ነው ብለዋል፡፡

እንደ አስተባባሪው ገለጻ፤ በክልሉ በዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ከ13 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ችግኞችን ለመትከል የታቀደ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ እስካሁን ወደ ሰባት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ማሳካት ችሏል፡፡ ይህም ከሦስት ሺህ ሄክታር መሬት በላይ መሸፈን የቻለ ነው፡ ፡ በጠቅላላው ከዓመታዊ እቅዱ 80 በመቶው ያህሉ ተሳክቷል፡፡

የክልሉን አግሮ ኢኮሎጂ ባህሪ መነሻ በማድረግ ከሚያዝያ ጀምሮ ያለውን የዝናባማ ወቅት በመጠቀም ብዛት ያላቸው ችግኞች መተከላቸውን፤ በዚህም እስካሁን የአካባቢውን መልከዓ ምድር ታሳቢ ያደረጉ የደን ችግኞች መዘጋጀታቸውን፤ ይህም የተጎዱ መሬቶችን ለማከም እንደሚረዳ ገልጸዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር የግብርና ውጤቶች የሆኑና ለምግብነት የሚያገለግሉ ችግኞች በስፋት ተዘጋጅተው እንደሚተከሉ ጠቅሰዋል፡፡

ይህም የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድ ለአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው ብለዋል፡፡

ለከተሞችና ለመንገድ ዳር ውበት የሚውሉ እንዲሁም ለእንስሳት ምግብ የሚያገለግሉ ችግኞች

# በመስኖ ስንዴ ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ዘመን የመስኖ ስንዴን በሦስት ሚሊዮን ሁለት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ለማልማት ታቅዶ ሁለት ሚሊዮን 978 ሺህ 122 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል፡፡

በዚህም በዘንድሮው የምርት ዘመን በዘር ከተሸፈነው መሬት ውስጥ ሁለት ሚሊዮን 199 ሺህ 402 ሄክታር መሬት በባህላዊ እንዲሁም 741 ሺህ 304 ሄክታሩን በኮምባይነር በመሰብሰብ 106 ሚሊዮን 24 ሺህ 856 ኩንታል ምርት ተገኝቷል ብለዋል።

እንደ አቶ ኢሳያስ ገለጻ፤ የመስኖ ስንዴ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሲዳማ፤ ደቡብ-ኢትዮጵያ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች በስፋት ተመርቷል፡፡ በሶማሌ ክልል ከለማው 6 ሺህ 704 ሄክታር መሬት ውስጥ 6 ሺህ 145 ሄክታር መሬት በበጋ ዝናብ የለማ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በ2016 ምርት ዘመን በክልሎች ከሚለማው የመስኖ ስንዴ ውስጥ 26 ሺህ 800 ሄክታሩን በምርጥ ዘር ብዜት ለመሸፈን መታቀዱን ያስታወሱት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ እስካሁን 10 ሺህ 289 ሄክታር መሬት በምርጥ ዘር መሸፈኑን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ የግብርና ዘርፏን ለማዘመንና የግብርና ምርቶች ላይ እሴት በመጨመር ከዘርፉ የምታገኘውን ገቢ ለማሳደግ ጥረት እያደረገች ነው። የበጋ መስኖ ስንዴም ከተረጂነት ለመላቀቅ አንዱና አስፈላጊው ሥራ መሆኑ ታምኖበት በስፋት ወደሥራ ተገብቷል ሲል ሚኒስቴሩ መግለጹ የሚታወስ ነው።

# “ኢትዮጵያ በሚገባት ልክ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ገለጹ። የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለሀገር እድገትና ብልጽግና የሚያበቃ ዋነኛ መሳሪያ መሆኑንም ገልጸዋል።

የ2016 የክረምት ወራት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የንቅናቄ መድረክ ትናንት በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሲካሄድ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ እንደተናገሩት፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በተደመረ ጉልበት፣እውቀትና ክህሎት ዜጎች ሀገራቸውን የሚገነቡበት መንገድ ነው።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በብዝሃነት በደመቁ ሀገራት ለጋራ እድገትና ብልጽግና የሚያበቃ ዋነኛ መሳሪያ መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ ቀደም በበጎ ፍቃድ በተሰጡ አገልግሎቶች የማህበረሰቡ አንገብጋቢ ችግሮች መፈታት መቻሉን የገለጹ ሲሆን፤ በዘንድሮው ክረምትም ሚሊዮኖች ይደገፋሉ ብለዋል።

አነስተኛ በጀት ባለበት ሀገር በበጎ ፍቃድ ሥራዎች ላይ መሳተፍ ያስፈልጋል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተሩ፤ ኢትዮጵያ በሚገባት ልክ እንዳልተገኘች የሚያስብ ዜጋ ሁሉ በበጎ ፍቃድ ሥራዎች ላይ ሊሳተፍ ይገባዋል ብለዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የጋራ እሴቶች የሆኑትን ርህራሄ እና መተሳሰብን የሚያጎለብቱበት መሆኑን ጠቁመዋል።

የዘንድሮው የክረምት በጎ ፍቃድ መርሀ ግብርም በ14 መስኮች አገልግሎት የሚሰጥበት ሲሆን፤ 26 ቢሊዮን ብር የሚገመት አገልግሎት ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል።

አገልግሎቱ የማህበረሰቡን አንገብጋቢ ችግር ለመፍታት እንዲሁም ፍትሐዊና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥ የሚያስችል ኃይል መሆኑን ሚኒስትሯ ተናግረዋል።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል የሚመለከት ሲሆን፤ የጤና ድጋፍ ፣ ጾታዊ ጥቃትን ማውገዝና የጥቃት ሰለባዎችን መደገፍ ፣ ሕገወጥ የሰው ዝውውርን ማስቆም በበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች የሚካተቱ ጉዳዮች እንደሆኑም ገልጸዋል።

በመርሀ ግብሩ ላይ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማእረግ የዲሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ማእከል ኃላፊ አደም ፋራህ፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ፣ የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ፣የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም የሲቪክ ማህበረሰብ አመራሮች ተገኝተዋል።

መርሀ-ግብሩን የሰላም ሚኒስቴር፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የትምህርት ሚኒስቴር በጋራ ያዘጋጁት ሲሆን፤ 20ሺ የሚሆኑ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም ወደ ተለያዩ ክልሎች በመሄድ አገልግሎቱን እንደሚሰጡ ገልጸዋል።

# የኮሪደር ልማቱ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እስከ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ በመገናኛ ወደ ሲኤምሲ፣ ከቦሌ ተርሚናል ወደ ጎሮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ወሎ ሰፈር፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ኤምባሲ ወደ አራት ኪሎ የሚወስዱ ኮሪደሮችን የሚያጠቃልል ነው።

ከእነኝህም መካከል ከአራት ኪሎ እስከ ራስ መኮንን ድልድይ ያለው መንገድ ተጠናቆ ለትራፊክ ክፍት ተደርጓል።

በዚህ የኮሪደር መንገድ ቀን ከወጣላቸው ስፍራዎች አንዱ የ100 ደረጃ ነው።ይህ ስፍራ ታሪካዊ ከመሆኑም ባሻገር በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች የሚዝናኑበት ስፍራ ነበር። ሆኖም ከስፍራው ታሪካዊነት አንጻር በአግባቡ እንዳልተያዘና ያልተገቡ ተግባራትን ማከናወኛ ሆኖ እንደነበር ይነገራል። አሁን ላይ አካባቢው እጅጉን ተቀይሯል፤ ይህንን ገጽታ የቀየረውም የኮሪደር ልማቱ ነው።

በአሁኑ ወቅት ከደረጃዎቹ ባሻገር ከጎኑ የተሠራው የማረፊያና የመዝናኛ ስፍራ መንፈስን ያድሳል። በእያንዳንዱ ደረጃ ላይም መብራት ተገጥሞለት ለአካባቢው ድምቀትን አላብሷል። በደረጃው ግራና ቀኝም ፋውንቴን ተዘጋጅቷል። እንዲሁም ስፍራውን በአረንጓዴ ተክሎች በማስዋብና ማረፊያዎችንም ጭምር በማመቻቸት ለአካባቢው ውበትና ለነዋሪዎችም ምቾትን በሚሰጥ መልኩ ተሰናድቷል።

የ80 ዓመት የእድሜ ባለጸጋው አቶ አክሊሉ አበበ ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ ነው። ከልጅነት እስከ እውቀት በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ተዘዋውረው ቃኝተዋል። አዲስ አበባን ከጫፍ እስከ ጫፍ ያውቋታል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታ ለውጦችን መመልከት ጀምረዋል። ታዲያ እየመጣ ያለው ለውጥ ለአካባቢው ማህበረሰብ ጽዱና ምቹ የመኖሪያ ከባቢን ከመፍጠር አልፎ ከውጭ ለሚመጡ ዜጎችም አምሮና ደምቆ መታየቱ ለሁላችንም ኩራት ነው ይላሉ።

የ70 ደረጃና አካባቢው ከዚህ ቀደም አንገት የሚያስደፋ ስፍራ መሆኑ ቀርቶ አሁን በተሠራው የልማት ሥራ እዩኝ ጎብኙኝ እያለ በመሆኑ ይህንን ማበረታታት ያስፈልጋል የሚሉት አቶ አክሊሉ፤ በሌሎች የዓለም ሀገራት ላይ የሚታዩ የልማት ሥራዎችን በሀገራቸው መመልከት በመቻላቸው እንደተደሰቱም ይናገራሉ።

አቶ አክሊሉ፤ “በአሁኑ ወቅት አስደሳችና ተስፋ የሚሰጡ ልማቶች እየተከናወኑ ነው። እነኝህ የልማት ተግባራት በዚህ ብቻ ሳይቆሙ ያረጁና ለኑሮ የማይመቹ ስፍራዎች በሌሎችም አካባቢዎች በመኖራቸው ያለውን ጅምር እንደማሳያ በመውሰድ በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ማስፋፋት አስፈላጊ እንደሆነ አንስተዋል።

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፤ ታሪካዊ ስፍራዎችን በመጠበቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ መንግሥት ለያዛቸው ውጥኖች መሳካትና እያከናወናቸው ላሉ መልካም ተግባራት ዜጎች ተባባሪና ፍቃደኛ መሆን መቻላቸው የሚበረታታ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

መንግሥት እነኝህን የልማት ሥራዎች ሲያከናውን እግረ መንገዱን የዜጎችን አንድነት፣ ሰላምና ደህንነት በማስጠበቅ ዜጎች ከቤታቸው በሰላም ወጥተው ያለምንም የጸጥታ ስጋት እንዲገቡ ማድረግ ቢቻል መልካም መሆኑንም አቶ አክሊሉ ይጠቁማሉ።

ሌላው አስተያየት ሰጪ አቶ ፍቅሩ ሀብተማርያም ውልደታቸውና እድገታቸው እዚሁ አዲስ አበባ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አከባቢ ነው። ከጓደኛቸው ጋር እየተሠራ ያለውን የኮሪደር ልማት ለመቃኘት 100 ደረጃ እንደተገኙ ይናገራሉ። አቶ ፍቅሩ አካባቢውን ከዚህ ቀደም ጠንቅቀው ያውቁታል። በጉርምስናቸው ወቅትም 40 እና 70 ደረጃዎች ላይ ማልደው በመነሳት የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ሠርተዋል።

“በመዲናዋ እየተሠራ ያለው የልማት ሥራ አሁን ላለውም ሆነ ለሚመጣው ትውልድ ትልቅ ሞራል የሚሰጥ ነው። በዚሁ ልክ አጥፊ ከመጣ በቀላሉ ሊጠፋ የሚችል በመሆኑ ዜጎች ከመንግሥት ጎን ሆነው ልማቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ሊያደርጉ ይገባል” ሲሉም አቶ ፍቅሩ ይጠቁማሉ።

የ76 ዓመቱ አዛውንት አቶ ፍቅሩ ፍቅርንና ሰላምን ይስጠን እንጂ ገና ብዙ እናያለን፤ መጪው ትውልድም ያማረችና የተዋበች ሀገር እንደሚረከብ አንስተው፤ ልማቱ የሀገር ውስጥና የውጭ ዜጎች የቱሪስት ፍሰትን በማሳደግ፣ ዜጎች በጽዱ አካባቢ እንዲኖሩ በማድረግ፣ የትራንስፖርት ፍሰትን በማሳለጥ ለአካባቢው ማህበረሰብም ሆነ ለሀገር እድገት በርካታ ጠቀሜታዎችን ይዞ እየመጣ ነው ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ሁሉም ዜጋ ለሀገር እድገት በሚችለውና ባለው አቅም የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይገባል ያሉት አቶ ፍቅሩ፤ ዜጎች በሌሎች የዓለም ሀገራት በመሄድ ገንዘብ አውጥተው እንደነኝህ አይነት ጽዱ ስፍራዎችን እንደሚጎበኙ ገልጸዋል። እየተሠራ ያለው የልማት ሥራ ሁሌም ጠብቁኝ የሚልና ከጊዜ ወደጊዜ ለውጥን የሚፈልግ በመሆኑ ዜጎች በባለቤትነት ስሜት ሊጠብቁት እንደሚገባም አጽንኦት ሰጥተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሪፖርቱ፣ የበጀት አጠቃቀምና ቁጥጥር ሂደቱን በወጉ እንዲጤን የሚያነቃ ነው!

በጀት ለአንድ ሀገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አጠቃላይ ሁለንተናዊ ብልጽግናን እውን ከማድረግ አኳያ የሚኖረው ሚና ተኪ የሌለው ነው፡፡ የሀገራት የእድገት መንገድ የሚለካውም የኢኮኖሚ አቅማቸው በሚፈቅድላቸው ልክ በሚመድቡት በጀት እና በጀቱን በተገቢው መልኩ ተጠቅመው በሚያሳዩት ውጤት ነው፡፡

በዚህ ረገድ በጀታቸውን በአግባቡ የተጠቀሙ ሀገራት የእድገታቸውን ምጣኔ ሲያፋጥኑ የመታየታቸውን ያህል፣ የሚመደበውን በጀት ላልተገባ ዓላማና ጥቅም የማዋል አዝማሚያ የሚታይባቸው ሀገራት በሙስናና ብልሹ አሠራራቸው ምክንያት ኢኮኖሚያቸው በሚታሰበው ልክ ሳይሆን የመቅረቱ ጉዳይ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

ኢትዮጵያም እንደ ሀገር ባልተቆራረጠው የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደቷ ውስጥ ኢኮኖሚዋ የሚያመነጨውን ገቢ በመሰብሰብ፣ እንዲሁም ብድርና ርዳታን ማዕከል በማድረግ በየዓመቱ ለምታከናውነው ሀገራዊ ሥራ በጀት እየመደበች እዚህ ደርሳለች፡፡ ይሁን እንጂ ይሄንን በጀት በአግባቡ ጥቅም ላይ አውሎ የሚፈለገውን ውጤት ከማምጣት አኳያ ችግሮች መታየታቸው አልቀረም፡፡

ምክንያቱም አይነትና መጠኑ ይለያይ እንጂ በጀትን በአግባቡ እና በቁጠባ ተጠቅሞ የተሰጠን ተልዕኮ ከማሳካት አኳያ በተቋማት የሚታዩ ችግሮች አሉ፡፡ ይሄም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በየዓመቱ በሪፖርት የሚገልጸው ሀቅ ነው፡፡ ከትናንት በስቲያ (ሰኔ 11 ቀን 2016 ዓ.ም) የፌዴራል ዋና ኦዲተር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው ፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርትም ይሄንኑ እውነት ያመላከተ ሆኗል፡፡

በዚህ ሪፖርት እንደተመላከተው፣ እንደ ሀገር የታለሙ ሁሉን አቀፍ ተግባራት ማስፈጸሚያ ይሆን ዘንድ ለ2014 የተመደበው በጀት ላይ የኦዲት ተግባር የተከናወነ ሲሆን፣ በዚህም በጀቱን ለታለመለት ዓላማ ከማዋል ባሻገር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ በዚህም ከገቢ አሰባሰብ ጀምሮ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ ያለአግባብ ክፍያ፣ መመሪያን ያልተከተለ ግዢ፣ እና ያልተወራረደ ውዝፍ ሂሳብን አለማስመለስን የመሳሰሉ ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

ለአብነትም፣ ከትናንት በስቲያ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የ2015 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት እንዳመለከተው፣ በ2014 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት በተከናወኑ የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ተደርጓል፡፡

በዚህም በ92 መሥሪያ ቤቶች ተመላሽ እንዲደረግ ተብሎ አስተያየት ከተሰጠበት 443 ሚሊዮን 23 ሺህ 846 ብር እና 23ሺህ 230 ዶላር ውስጥ ተመላሽ የተደረገው 11 በመቶው ብቻ ነው፡፡ በተመሳሳይ በ2014 በጀት ዓመት የተሟላ ማስረጃ ሰነድ ካልቀረበበት ብር አምስት ቢሊዮን 61 ሚሊዮን 185 ሺህ 100 ብር ውስጥ 10 በመቶው ብቻ ነው ማስረጃ የቀረበለት፡፡

በሌላ በኩል፣ የጥሬ ገንዘብ ጉድለትን ለመመልከት በተደረገ የኢዲት ሥራ በ2 መሥሪያ ቤቶች 383ሺህ 238 ብር የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተም በ124 መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ከ14 ቢሊዮን 119 ሚሊዮን ብር በላይ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ከወጪ አሠራር አኳያም፣ በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ሕጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ11 መሥሪያ ቤቶች ከ43 ሚሊዮን 545 ሺህ ብር በላይ ምንም አይነት ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ገንዘብ ተገኝቷል፡፡ በተመሳሳይ በ30 መሥሪያ ቤቶች 16 ሚሊዮን 407 ሺህ 985 ብር ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ ተከፍሏል፡፡

በ32 መሥሪያ ቤቶች እና በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች፣ እንዲሁም ለውሎ አበልና ለሌሎች ወጪዎች በሚል 62 ሚሊዮን 683 ሺህ 793 ብር ያለአግባብ በብልጫ ተከፍሏል፡፡ በ73 መሥሪያ ቤቶችና በ15 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ከሁለት ቢሊዮን 199 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ ተፈጽሟል፡፡

እነዚህን እና መሰል የዚህ ኦዲት ግኝት ደግሞ፣ ወደ አንድ ትሪሊዮን የሚጠጋ ሀብት ለተበጀተለት የ2017 በጀት ዓመት የበጀት አጠቃቀም ሂደት ትልቅ ግብዓት ሊሆን የሚገባው ሲሆን፣ በዚህም ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት ሕግና አሠራርን ተከትለው ሥራ ላይ ለማዋል የሚችሉበትን ተቋማዊ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲዘጋጁ የሚያደርግ፣ ምክር ቤቱም ይሄንኑ ማዕከል አድርጎ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓቱን እንዲከውን ግንዛቤን የሚያሳድግለት ነው፡፡

ሪፖርቱ በቀረበበት ወቅት ከምክር ቤቱ “በሕገ-መንግሥቱ እና በምክር ቤቱ የአሠራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ላይ እንደተመላከተው፣ ምክር ቤቱ በጀት ማፅደቅ ብቻ ሳይሆን፣ የፀደቀው በጀት በተገቢው አሠራር፣ ቁጠባን መሠረት ባደረገ መልኩ ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉና ውጤታማ ስለመሆኑ የመከታተል መብትና ግዴታውን መወጣት አለበት፣ ተቋማትን የሚከታተሉ ቋሚ ኮሚቴዎችም በዚሁ መንፈስ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፣” በሚል የተነሳው ሃሳብም ይሄንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎቹ ተስፋና ስጋት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ዓለም በነዳጅ ከሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ጥገኝነት በመውጣት በኤሌክትሪክ ወደሚሰሩ ተሽከርካሪዎች መጠቀም እያደረገ ያለውን ግስጋሴ ቀጥሏል። በዚህም ዋጋው በየጊዜው እየጨመረ ከመጣው እንዲሁም በአካባቢ ብክለት ተጠቃሽ ከሆኑት መካከል አንዱ ከሆነው ነዳጅ እየተላቀቀ ነው።

በሀገራዊ ዕድገት ላይ ትልቅ አቅም እንዳላቸው የሚነገርላቸው እነዚህ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በተለይ ለአፍሪካ ሀገራት ሰፊ ዕድል ይዘው መምጣታቸው ይገለጻል። አፍሪካ በዓለም ላይ ፈጣን ዕድገት እያስመዘገቡ ካሉ ገበያዎች አንዷ መሆኗ ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኢንዱስትሪው መስፋፋት ከፍተኛ እድሎችን የሚፈጥር ይሆናል። የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በተለይም ብክለትን የሚቀንሱ እና ኃይል ቆጣቢ መጓጓዣ በመሆናቸው ወደፊት እጅግና ተፈላጊ እንደሚሆኑም ይታመናል።

በአሁኑ ወቅትም ብዙ የአፍሪካ መንግሥታት ማበረታቻዎችን በማቅረብና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ተጠቃሚዎችንና የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኢንዱስትሪዎችን እየደገፉ ይገኛሉ። የኤሌክትሪክ ተከርካሪዎች ብዙ ፈተናዎች እየገጠሟቸው ቢሆንም፣ የአፍሪካ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኢንዱስትሪ በመጪዎቹ ዓመታት ያድጋል ተብሎ እንደሚጠበቅም መረጃዎች ይጠቁማሉ። በ2030 በአፍሪካ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ገበያ 100 ቢሊዮን ዶላር ሊደርስ እንደሚችል አንዳንድ ግምቶች ያመለክታሉ።

እ.አ.አ ከ2019 ጀምሮ የኤሌክትሪክ መኪኖች በዓለም አቀፍ ደረጃም እንዲሁ ቁጥራቸው በከፍተኛ ጭማሪ እያሳየ መጥቷል። መረጃዎች እንዳመለከቱት፣ በአሁኑ ወቅት በመላ ዓለም ከ25 ሚሊዮን በላይ የኤሌክትሪክ መኪኖች ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥም አብዛኞቹ የሚገኙት በቻይና ነው። ከዓለም የኤሌክትሪክ መኪኖች 60 በመቶ ያህሉም የተመረቱት በቻይና ነው።

ኢትዮጵያም ይህንኑ ጉዞ በመቀላቀል አያሌ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች በአውራ ጎዳናዎቿ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ላይ ትገኛለች። ሀገሪቱ በከፍተኛ መጠን እያለማች የምትገኘውን እምቅ ታዳሽ ኃይል ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎቹም በማዋል ለነዳጅ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማዳን እየቻለችም ነው።

ተሽከርካሪዎቹ በተለያዩ አማራጮች ወደ ሀገሪቱ የሚገቡ ሲሆን፣ የግል ባለሀብቶችም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ መገጣጠም ጀምረዋል። ከአንድ መቶ ሺ በላይ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች በሀገሪቱ እየተንቀሳቀሱ መገኘታቸውም ይህንኑ ያመለክታል።

ዘርፉ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገቡ ላሉ ሀገራት ማስፈንጠሪያ እንደሚሆን ይጠበቃል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በአንድ ወቅት የኤሌክትሪክ መኪና በብዙ መልኩ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ቴክኖሎጂ መሆኑን ሲገልጹ፣ “ይህቺ ሀገር ኤሌክትሪክ የማምረት አቅም አላት። ከወዲሁ ይህንን መኪና (የኤሌክትሪክ) መገጣጠም እና ማምረት ከጀመርን የዛሬ አምስት እና አስር ዓመት የምንመኛትን፣ የበለጸገች ሀገር ለማየት ይቻላል” እንዳሉትም ተሽከርካሪዎቹ በስፋት በመጠቀም እድገቱን ለማረጋገጥ መስራት ይገባል።

የዓለም ጉዞ ወደ ኤሌክትሪክ መኪኖች ባጋደለበት በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን መጠቀም የሚያስችል ፖሊሲ ተግባራዊ ከመሆን ባለፈ በማህበረሰቡ ዘንድ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን የመጠቀም ፍላጎት ከፍ ማለቱ እንደ ሀገርም እንደ ማህበረሰብም ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

የእነዚህ መኪኖች በሀገሪቱ ሥራ ላይ መዋል የነዳጅ ወጪን ከመቀነሱ በተጨማሪ ሀገሪቱ በአየር ንብረት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ብክለት በተወሰነ መልኩም እንድትቀንስ ያስችላታል። የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎቹ ድምጽ አልባ መሆናቸውም በድምጽ ብክለት በኩል ሊመጣ የሚችል ችግር እንዳይኖር ያደርጋል።

በእነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች በሀገሪቱ ተሽከርካሪዎቹ በከፍተኛ ሁኔታ ተፈላጊ እየሆኑ መጥተዋል፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ በኤሌክትሪክ መኪና ፍላጎት ከቀዳሚዎቹ ሀገራት ተርታ መሰለፏም እየተገለጸ ነው።

የአየር ንብረትን በከፍተኛ ደረጃ የሚበክል ካርበን የሚለቁ አሮጌ መኪኖች በብዛት የሚነዱባት ሀገር፣ የታዳሽ ኃይል ልማት ሥራን አጠናክራ በመቀጠል የኤሌክትሪክ መኪኖችን ለመጠቀም የጀመረችው ጉዞ ፈጣን የሚባልም ነው።

እነዚህ ሁሉ መልካም አጋጣሚዎች ተሽከርካሪዎቹን ከውጭ ለሚያስመጡ ድርጅቶችና ግለሰቦች መልካም አጋጣሚ እየፈጠረላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ፣ የግሉ ዘርፍ እነዚህን በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ መገጣጠም ውስጥ እንዲገባም አስችሎታል። ይህም ለኢንቨስትመንቱ ዘርፍና ከዘርፉ ለሚገኘው ቱሩፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ነው።

መንግሥትም በዘርፉ ላይ በትኩረት እየሰራ መሆኑ ይታወቃል። ለእዚህም በኢትዮጵያ የትራንስፖርት ዘርፍ በ10 ዓመት ዕቅድ ውስጥ ለታዳሽ ኃይል ቅድሚያ መሰጠቱ አንድ ማሳያ ነው። በዚሁ መነሻና ዕቅድም በአሁኑ ወቅት በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የሕዝብ ማመላለሻ እና አነስተኛ ተሽከርካሪዎች በብዙ ቁጥር ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ታቅዷል። በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መኪና ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚጣለው ግብርም እንዲሁ ዝቅ መደረጉ ተሽከርካሪዎቹ በስፋት ወደ ሀገሪቱ እንዲገቡ የሚያበረታታ እንደሆነ ይታመናል።

እንደሚታወቀው የኤሌክትሪክ መኪኖቹ በዋናነት የሚፈልጉት የኤሌክትሪክ ኃይል ነው። ይህን ኃይል ለማግኘት ደግሞ መኪኖቹ ቻርጅ መደረግ ይኖርባቸዋል። ቻርጅ የሚደረጉባቸው መንገዶች ሁለት አይነት ናቸው። ፈጣን/ፋስት/ እና ፈጣን ያልሆነ በሚል ይታወቃሉ። ፈጣን የሚባለው በ30 ደቂቃ ውስጥ ቻርጅ የሚያደርገው ነው። ሌላኛው ዘለግ ያለ ጊዜን የሚፈልገው ነው።

የኤሌክትሪክ መኪኖቹ በስፋት ወደ ሀገሪቱ እንዲገቡ መደረጉ ትልቅ ነገር ሆኖ የቻርጅ ጉዳይ ግን ስጋት እየሆነ ይገኛል። ኃይል መሙያ መሠረተ ልማቶች/ ቻርጅ ማድረጊያ ቦታዎች/ እንደልብ አለመኖራቸው ለቴክኖሎጂው መስፋፋት ስጋት ሆኗል። ቻርጅ ማድረጊያዎች በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች እንደልብ አይገኙም፣ ከአዲስ አበባ ውጪ ደግሞ ፈጽሞ የሚታሰቡ አልሆኑም።

መኪኖቹ እንደ አፍሪካም ስጋቶች አሉባቸው። ከነዳጅ ወይም ከናፍጣ ተሽከርካሪዎች የበለጠ ውድ መሆናቸውና አፍሪካ ውስጥ ብዙዎች ሊገዟቸው የማይችሉ መሆኑ ተሽከርካሪዎቹን በስፋት ጥቅም ላይ በማዋል በኩል አንድ ችግር ሆኗል።

ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የመሠረተ ልማት አውታር አለመሟላትም እንዲሁ አንዱና ዋነኛው እንቅፋት እንደሆነም መረጃዎች ያሳያሉ። በኢትዮጵያ የተሽከርካሪዎቹ አንዱ ፈተናም ይሄው ነው። የቻርጅ ማድረጊያ ስፍራ እንደ ልብ አለመኖር ፈተና ሆኗል።

ኢትዮጵያ ውስጥ እነዚህ ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱባቸው የኃይል መሙያ መሠረተ ልማቶች ልክ እንደ ነዳጅ ማደያ ሁሉ በተለያዩ ስፍራዎች ላይ መገኘት ይኖርባቸዋል። እነዚህን የኃይል መሙያ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ በማድረግ በኩል ትልቅ ኃላፊነት ያለበት የኢትዮጵያ ነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ስለመሆኑ ይገለጻል። ድርጅቱ በእዚህ ጉዳይ ላይ ረቂቅ ሕግና መመሪያ በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማድረጉ ተጠቁሟል፣ ይሁንና እስካሁን መመሪያውን አዘጋጅቶ በማጠናቀቅ ወደ ሥራ እንዲገባ አላደረገም።

ባለስልጣኑ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ኃይል መሙያ መሠረተ ልማትና ታሪፍ ቀደም ተብሎ መሟላት ያለበትና የዘገየ ስለመሆኑ በማመን በአጭር ጊዜ ውስጥ የኃይል መሙያ መሠረተ ልማቱ እንደሚሟላና ታሪፍም የሚወጣለት መሆኑንም ከሰሞኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ባደረገበት ወቅት ጠቁሟል።

ተሽከርካሪዎቹ ወደ ሀገሪቱ ከመግባታቸው አስቀድሞ መሠራት ያለበት ሥራ ያልተሠራ መሆኑ የተመለከተ ሲሆን፣ ተሽከርካሪዎቹ በግለሰብ ደረጃ እንዲሁም በተለያዩ አማራጮች ኃይል እያገኙ መሆናቸው ተገልጿል። ለመንቀሳቀስ የሚያስፈልጋቸውን ኃይል ሕጋዊ በሆነ አሠራርና መመሪያን መሠረት ባደረገ መልኩ በአዲስ አበባ ከተማና በክልል ከተሞች ጭምር ተደራሽ መሆን እንዳለባቸው አጠያያቂ ባይሆንም፣ ይህ ሲሆን ግን አልታየም።

በአሁኑ ወቅት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎቹ እያጋጠማቸው ከሚገኘው የኃይል መሙያ መሠረተ ልማት ችግር በተጨማሪ ሌሎች ስጋቶች እንዳሉባቸው ቢገለጽም፣ ዘርፉ ብዙ እድሎችን ይዞ የመጣ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተሽከርካሪዎቹ ብዛት መጨመሩን ቀጥሏል። በችግሮች ውስጥም በመሆን የተሽከርካሪዎቹ ብዛት መጨመሩንም እንደ መልካም አጋጣሚ መጠቀም ይገባል።

ይህ በራሱ አንድ እድል ነው፣ ይህን በሚገባ ለመጠቀም መሠራት የሚገባቸው የቤት ሥራዎችን በፍጥነት መሥራት ይገባል። በተለይ የኃይል መሙያ መሠረተ ልማት ለማሟላት የግል ባለሀብቶችና የተሽከርካሪ ባለቤቶች የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ ሲሆን፣ መንግሥትም የጉዳዩ ባለቤት በመሆን ይህን ጥረት በሚችለው ሁሉ መደገፍ ይኖርበታል።

ከዚህ በተጨማሪም በሌሎች መኪኖቹን በስፋት በሚጠቀሙ እንደ ቻይና ባሉ ሀገሮች የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት ሥራ ላይ የዋሉ መንገዶችን በማጥናት እንዲተገበሩ ማድረግ ላይም መሥራት ይኖርበታል። አሁን የሚታዩትን ችግሮች መፍታት ላይ ብቻ ማተኮር ሳይሆን በቀጣይ ሊገጥሙ የሚችሉ ችግሮች የሚፈቱ ሥራዎች ከወዲሁ መሠራት ይኖርባቸዋል እንላለን።

# ተስፋ ሰጪው በምግብ እህል ራስን የመቻል ጉዞ

**ታሪኩ ዘለቀ**

በዓለም ላይ ግብርና ትልቁና ዋነኛው የሀገራት ኢኮኖሚ መሰረት ነው። ጠንካራ አቅም የገነቡ ሀገራት ለግብርና ምርትና ምርታማነት የሰጡት ትኩረት ውለታው ይከፍላቸዋል። የኢኮኖሚ ፖሊሲያቸው ማጠንጠኛ ግብርና እና ግብርና የሚል ነው። መርሀቸው ከፍጆታ ወደ ሸመታ የሚቀርብ፣ በምግብ ራስን የመቻል እሴትን ጨምሮ በግዙፍ የማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች እድገትን ማሳለጥ ነው።

በዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት /ፋኦ/ ትርጓሜ መሰረት የምግብ ዋስትና ተረጋገጠ የሚባለው በአንድ ሀገር ያሉ ሁሉም ዜጎች ሁልጊዜ ንቁና ጤናማ ሆነው ለመቆየት የሚያስችላቸውን በቂ፣ ንፁህና የተመጣጠነ የምግብ አማራጭ ለማግኘት የሚችሉበት የኢኮኖሚ አቅምና አቅርቦት ሲኖራቸው ነው።

የምግብ ዋስትና አንድምታው የራስን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የውስጥን ፍጆታን ከመሙላት የዘለለ ነው። የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ማለት የምግብ ምርትን በማሳደግ የምርት መውደቅና የዓለም አቀፍ ገበያ አሉታዊ ተፅዕኖ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንኳ ለዜጎች በቂ የምግብ ምርት ሳይስተጓጎል የሚያቀርብ፣ የምርት፣ የግብይትና የመጠባበቂያ ክምችት መዘርጋት ነው።

‹‹በምግብ ራስን መቻል ከማምረት በላይ›› በሚል የኢትዮጵያ መንግስት ባለፉት ዓመታት በተለይ በስንዴ ምርትና ምርታማነት አስደናቂ ውጤትን እያስመዘገበ ይገኛል። ለእርዳታ እጇን ትዘረጋ የነበረች ሀገርም የተሻለ ምርት አምራች የሚል ስም ተለጥፎላት እውቅና ማግኘቷ ይበል የሚያሰኝ ነው።

ባለንበት ዘመን በምግብ ራስን መቻል ከሉአላዊነት ጋርም በቀጥታ የሚያስተሳስሩት በርካቶች ናቸው። ለዚህ በእርዳታ ሰበብ ፖለቲካቸውን የሚያቀብሉ ሀገራት መብዛታቸው ራስን መቻል ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ያስረዳል።

ዛምቢያዊቷ ኢኮኖሚስት ዳምቢሳ ሞዮ ‹‹Dead aid: Why aid is not working and how there is a better way for Africa›› የሚል ርዕስ በሰጠችው ቆየት ያለ መፅሀፏ በዕርዳታ ሰበብ አፍሪካን የተጣቧትን የምዕራባዊያን ሴራ ተንትና አቅርባለች። በመፅሀፉ የሚነሳው ሀሳብ ከዕርዳታ ያልተላቀቀ ማኅበረሰብ መፍጠር የተረጂነት ስነልቡናን ማንገስ፤ ራስን መቻል ብርቅ እስከሚሆን ድረስ በማሳየት ይህንን ትርክት እንደመርፌ መውጋት ነው።

በምግብ እህል ራሷን የቻለች ሀገር ኢኮኖሚዋ እንዳደገ ጭምር የምትቆጠር ነች። እናም ግብርና በምግብ እህል ራስን ለመቻል ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚውም ሆነ ለሌላው ነገር መሰረት ለሆኑባት ኢትዮጵያ ደግሞ ትልቅ ትርጉም ይሰጠዋል።

በሀገራችን ግብርና ዋነኛው የኢኮኖሚ መሰረት ሆኗል፤ አሁንም ነው። በዓለም ግብርና ከአስር ሺህ ዓመታት የተሻገረ ታሪክ እንዳለው ይነገርለታል። ስንዴ ደግሞ ዋናው ሰብል ነው። ይሁን እንጂ የፖለቲካ ሰብል በመባል የሚታወቀው ስንዴ፣ በምግብ ጥያቄ የዓለም መሳሪያ በሆነው ስንዴ ራሳችንን ባለመቻላችን ረሀብተኛ ከሚለው ስያሜያችን ጀምሮ ዓለማቀፍ ጫናዎችን ስንሸከም ቆይተናል።

ኢትዮጵያ ከፍጆታዋ ከ25 እስከ 30 በመቶ የሚሆነውን ዓመታዊ የስንዴ ፍላጎቷን ለማሟላት ለዓመታት በየዓመቱ ከ700 ሚሊዮን ዶላር እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር ለስንዴ ግዢ ስታወጣ ቆይታለች። ታሪክ ተቀየረና በኢትዮጵያ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማትን በማስፋፋት ስንዴ በየዓመቱ የሚመረትበት ወቅትን በመጨመር በ2014 የስንዴ ፍጆታዋን ሙሉ በሙሉ ሸፍና በየካቲት 2015 ዓ.ም ደግሞ ስንዴ ወደ ውጪ መላክ ጀመረች።

ይህ ጥረት የኢትዮጵያን ገፅታን የሚለውጥ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ሆነ። ዓለምም ይህን ጥረትና የተገኘውን ፍሬ አደነቀ። ይህ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ዓለማቀፍ አካላት ጭምር ዕውቅናን ማግኘት ጀምሯል። ሀገሪቱ በጀመረችው አስደናቂ የስንዴ ምርት ልማት ከተገኙ ውጤቶች መካከልም በ2010 በስንዴ ምርት ይሸፈን የነበረው 50 ሺህ ሄክታር የስንዴ እርሻ በ2013 ወደ 167 ሺህ ሄክታር አድጓል።

በ2014 መጀመሪያ ላይ ደግሞ ወደ 650 ሺህ ሄክታር ማደጉን መረጃዎች ያሳያሉ። በ2015 ደግሞ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መድረስ ችሏል። ከዚህም 47 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ መሰብሰብ ተችሏል። ዘንድሮ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለመሸፈን በዕቅድ ተይዞ እንደነበር ተገልጧል።

የኢትዮጵያ መንግስት ለግብርናው ዘርፍ የሰጠው ትኩረት ምርትና ምርታማነት ተስፋ ሰጪ ውጤት እየተገኘ እንደሆነ እየተመለከትን ነው። በበጋ መስኖ ልማት በርካታ ክልሎች ካለፉት ዓመታት አንፃር የተሻለ ምርት እያመረቱ ይገኛሉ። ለግብርናው ዘርፍ ቅድሚያ በመስጠት በስንዴና በሩዝ ምርት ስኬታማ ውጤቶች እየተመዘገቡ ይገኛል። የሜካናይዝድ እርሻም እየተስፋፋ መጥቷል።

በሰው ኃይል ጉልበትና ልፋት ላይ የቆየው የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ እምብዛም ለውጥ ሳታይበት ዘመናት አልፈዋል። ለዚህም ነው መዋቅራዊ ማሻሻያዎችን በማድረግ ወደ ስራ ተገብቶ የሚጨበጥ ለውጥ ማምጣት የተቻለው ይላሉ የግብርና ሚኒስትሩ ዶክተር ግርማ አመንቴ። ከሞፈርና ቀንበር ወደ ማሽን በማሸጋገር ሰፊ ስራ ተሰርቷል። በቅርብ ዓመታት ብቻ ከ5 መቶ በላይ ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ተደርጓል።

እንዲህ መደረጉን ገበሬዎቹም ያምናሉ። ቀደም ባሉ ዓመታት በበሬ ያርሳሉ በበሬ ይሰበስባሉ። አሁን ከዘር እስከ ምርት መሰብሰቢያ ጊዜ ዘመናዊ መሳሪያዎችን መጠቀማቸው በምርት ግኝትም የተሻለ፣ በኑሯቸውም ለውጥ ያመጣ መሆኑን ይናገራሉ።

ቀደም ባሉ ዓመታት የቅንጦት እቃዎች ከውጭ እንዲገቡ ቅድሚያ ይሰጥ ነበር። አሁን ግብርናውን በማዘመን በመካናይዜሽን መሳሪያዎች አቅርቦት የተሰራው ተግባር የሚታይ ሆኗል። ይህ ምርትን በማሳደግ ረገድ ያለው ሚና ከፍ ያለ ነው። ነገር ግን አሁንም የተሻለና የበለጠ ስራን ይጠይቃል።

በእርግጥም ከዚህ በፊት ባለሀብቶች መኪናዎችን ለማስገባት ከቀረጥ ነፃ እድል ያገኙ ነበር። ይህንን መሰል እድል አርሶ አደሩ አግኝቶ አያውቅም። የግብርና ዘርፉ ወደ ሜካናይዜሽን እንዲገባ የማበረታታት ተግባራት ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተጀመረ ተግባር ነው። ይህ ቀጣይነት ኖሮት ግብርናውን የመደገፍና የማበረታታት ስራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ከሆነ ተስፋ ሰጪ ጅምር እየታየ ነው።

በሀገራችን ምጣኔ ሀብት ለውጥ እንዲመጣ ከተሰራው መዋቅራዊ ማሻሻያና በተግባር የታየው በግብርናው ረገድ ከፍ ያለ ነው። ምርትን ለማሳደግ የተሰራው በስንዴ፣ በሩዝና በሌሎች ምርቶችም ውጤት ማየት ተችሏል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ግብርና ከፍተኛ እመርታ አምጥቷል ማለት ያስደፍራል። ይህ አምናም ዘንድሮም በተግባር ታይቶ የተመሰከረለት ነው። የሀገሪቱን ዕድገት ተሸካሚ ሆኗል ማለት ያስችላል። ለስንዴ ሀገሪቱ በየዓመቱ 7 መቶ እና 8 መቶ የአሜሪካ ዶላር ታወጣ ነበር። ከአምና ጀምሮ ሀገሪቱ ለስንዴ አንድ ብር እንደማታወጣ መንግስት አሳውቋል።

ባለፉት 50 ዓመታት ስንዴ ከውጭ ስናስገባ ነበር። 2011 በመኸር የሚታረሰው የስንዴ መሬት 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ብቻ ነበር። ይህ ማለት በዝናብ ብቻ ነበር የምናርሰው ማለት ነው። ኢትዮጵያ ታገኝ የነበረው 48 ሚሊዮን ኩንታል ብቻ ነበር። በ2016 ዓ.ም የካቲት ላይ 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንደሚሸፈን ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ አሳውቆ ነበር።

ለውጡና እድገቱ በዚህ መልኩ የሚገለፅ ሆኗል። ምርታማነቱ ከ5 ዓመታት በፊት 27 ኩንታል በሄክታር የነበረው ስንዴ በ2015 ዓ.ም በነበረ መረጃ ወደ 39 ኩንታል በሄክታር ማግኘት ተችሏል።

ግብርናችን የሚታወቀው በተበጣጠሰና በአነስተኛ ማሳ ላይ የሚከወን ነው። ይህንን በመቀየር በአሁኑ ሰዓት 8 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በኩታገጠም የገበያ እሳቤ አርሶና አርብቶ አደሮቻችን በልቶ ለማደር ሳይሆን ለገበያ፤ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ እንዲያመርቱ ተደርጓል። ከ 9 ሚሊዮን ባላይ አርሶና አርብቶ አደር ተደራጅተው እየሰሩ ይገኛሉ።

ከተናጠል ይልቅ በኩታ ገጠም እንዲታረስ በማድረግም ምርታማነት እንዲጨምር፣ የአርሶ አደሩ ኑሮ እንዲሻሻል የተወሰደ ሌላ እርምጃ ነው። ኑሮን ማሻሻል ተገቢ ተደርጎ ገበያ ተኮር ምርትና የእርሻ ስራ ማከናወን ተመራጭም ተደርጓል።

በግብርናው ዘርፍ በተሰራው ስራ ውጤት ቢኖርም ፈተናዎች ነበሩበት። የግብአት አቅርቦት በዋናነት የሚነሳ ነው። ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ መሰል ችግሮችን በማስወገድ፣ ቅርብ ክትትል በማድረግ ምርትን ማሳደግ ዋና መፍትሄ ነው።

ከእኛ አልፎ ለውጪ ገበያ የቀረበ ስንዴ በሀገር ውስጥ ገበያ ዋጋው አልቀመስ ብሎ የዳቦ ዋጋ ከምንግዜውም በላይ ተወዶ ኢትዮጵያውያን ችግር ውስጥ መገኘታችን እሙን ነው። ስንዴን ከሀገሯ ፍጆታ ተሻግራ ለውጭ ገበያ ያቀረበች ሀገር ዜጎቿን ዳቦ በአግባቡ አለመመገብ ተቃርኖ በብዙ የግብይት ሰንሰለት ችግሮች የተተበተበ መሆኑን ያመላክታል።

ይህን ችግር መፍታትና የስንዴን የሀገር ውስጥ ዋጋ ማረጋጋት ላይ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል። ደግሞም በቀጣይ ኢትዮጵያ ለስንዴ ምርት የሚሆን የውሃ፣ የመሬትና የሰው ኃይል አቅም ያላት ሀገር በመሆኗ ይህንን ሀብት በሙሉ አቅም በመጠቀም ከተገኘው ውጤት በላይ ጠንካራ ስራ መስራት ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ከብሄራዊ ሉአላዊነት ጋር ያስተሳሰረችው ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። በስንዴ የታየው ስኬትም በሌሎች ሰብሎችም መድገም፣ የገበያ ሰንሰለቱን ማዘመን ደግሞ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋትም መፍትሄ ይዞ የሚመጣ ይሆናል። አርሶ አደሩም ለእርሻ ስራው በቂ ግብአት በወቅቱና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲደርሰው ማድረግም ከሁሉም ይጠበቃል።

> **ባለንበት ዘመን በምግብ ራስን መቻል ከሉአላዊነት ጋርም በቀጥታ የሚያስተሳስሩት በርካቶች ናቸው። ለዚህ በእርዳታ ሰበብ ፖለቲካቸውን የሚያቀብሉ ሀገራት መብዛታቸው ራስን መቻል ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ያስረዳል**

# ወቅታዊ

# ‹‹ሐረር ላይ አንዱ ለአንዱ ጌጥ ሆኖ በመኖሩ ትልቅ የቱሪስት መስዕብ እየሆነ ነው››

-አቶ ተወለዳ አብዶሽ

- የሐረሪ ባህል፣ ቀርስና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ



**ሙሉቀን ታደገ**

የሐረሪ ክልል ሁነኛ መታወቂያ እና ትልቁ ሀብት ቱሪዝም ነው። የክልሉ መንግስት እንዲሁም የባህል፣ ቅርስና ቱሪዝም ቢሮም ይህን በውል በመረዳት በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ እና ለማዘመን የሚያስችሉ በርካታ ስራዎችን እያከናወኑ ይገኛል።

ይህም ሐረርን በዓለም አቀፍ ደረጃ በቱሪዝም ዘርፉ ቀዳሚ እና ተወዳዳሪ እንድትሆን የሚያስችል ከመሆኑ ባለፈ ቀርሶችን ለትውልድ ጠብቆ ከማስተላለፍ አኳያ የሚኖረው ሚና የማይተካ ነው ።

በክልሉ እየተከናወነ ያለው ቅርሶችን መልሶ የማልማት ስራ የቱሪዝም ዘርፉን ከማሳደጉም ባሻገር ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር የቻለ ነው። ይህ የሐረሪ ክልል ተግባር ለሌሎች ክልሎች ተሞክሮ መሆን ስለሚችል በቱሪዝም ዘርፉ እየተከናወነ ያለውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? ስንል ከሐረሪ ባህል፣ ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ተወለዳ አብዶሽ ጋር ቆይታ አድርገናል፤ መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን ፡-የሐረሪን የቱሪዝም ጸጋ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ተወለዳ፡-** ሐረር የዓለም ስልጣኔ ማሳያ ጥንታዊት ከተማ ነች። የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ በርካታ ቅርሶችን በጉያዋ አቅፋም ይዛለች። ጀጎል እና ሸዋልኢድን የመሰሉ ቅርሶቿ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ በመሆናቸው የሰው ልጅ ሃብት ሆነው ተመዝግበዋል።

እነዚህን ቅርሶች ደህንነታቸውን ጠብቆ ለትውልድ ከማስተላለፍ አንጻር እንደ ክልል እና እንደ ቢሮ ልዩ ትኩረት ሰጥተን ስንሰራ ቆይተናል። እየሰራንም ነው። የሰው ልጅ ቅርስ የሆነውን ጀጎልን እንዲሁም በውስጡ ያሉ ትውፊቶችን እና ባህሎችን ከትውልድ ትውልድ ለማሸጋገር ሰፋፊ ስራዎችን እየሰራን ነው።

እንደ ቢሮ ጀጎልን ብቻ ሳይሆን ከጀጎል ውጭ የሚገኙ በገጠር እና በከተማ ያሉ የተለያዩ የቱሪዝም መስህቦችን ደህንነታቸውን አስጠብቀን ለትውልድ ለማስተላለፍ ልዩ ትረኩረት ሰጥተን ስንሰራ ነበር። እየሰራንም እንገኛለን።

በተለይ ከጀጎል ጋር ተያይዞ በርካታ ስራዎችን አከናውነናል። ለረጅም ጊዜ በሚባል ሁኔታ ጀጎል እና ዙሪያዋ በሕገወጦች የተወረረበት፤ ቅርሱ እየተበላሸ የነበረበት እንደዚሁም አደጋ ላይ የወደቀበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። የጀጎል መልሶ ማልማት ስራ በክልሉ ፕሬዚዳንት አነሳሽነት ከተጀመሩ ስራዎች አንዱ ነው።

የጀጎል ውስጥ ለውስጥ መንገዶች ባጣም ያረጁ፣ እንዲሁም ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ እና ቆሻሻ የበዛባቸው ነበሩ። በነገራችን ላይ የጀጎል መንገዶች ሁሉ ቅርስ ናቸው። ነገር ግን ከእንክብካቤ ጉድለት ከ40 ዓመታት በላይ የተዘጉ መንገዶችም ነበሩ። እነዚህ መንገዶች ከመዘጋታቸውም ባለፈ ሁሉም ሰው ቆሻሻ ይጥልባቸው ስለነበር የአካባቢውን ውበት ከማሳጣታቸውም በላይ የማኅበረሰቡን ጤና በከፍተኛ ሁኔታ ሲጎዱት ነበር።

ይህን ችግር ለመፍታት እንደክልል ቀን ከሌት ሰርተናል። በዚህም ቅርሱን ለትውልድ መሸጋገር በሚችልበት ደረጃ ማድረስ ችለናል። አሁን ላይ የጀጎል ግንብ ውስጥ እና ዙሪያው በአረንጓዴ ተሸፍኖ ለቱሪስቱ ሳቢ እና ማራኪ እንዲሆን፤ ለነዋሪው ደግሞ ምቹ የኑሮ ቦታ ማድረግ ተችሏል።

ቅርሱን ስናድስ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እና አሰራሮችን በመዘርጋት የመልሶ መልማት ስራ ሕዝባዊ የማድረግ እና የአመለካከት ለውጥም ማምጣት ተችሏል። ቀደም ብሎ ይህ ቅርስ ይታሰብ የነበረው የአንድ አካል እንደሆነ ነው። የጥበቃ እና የእንክብካቤ ስራውም ለመንግስት ብቻ የተተወ ነበር። ከዚህ እሳቤ ጋር ተያይዞ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣና ቅርሱ የሁላችንም ቅርስ ነው፤ ሁላችንም ልንጠብቀው ይገባል፤ እኔም ድርሻ አለኝ የሚል አስተሳሰብ እንዲኖር የተሰራበት እና ሁሉም በባለቤትነት እንዲሳተፍ ለማድረግ ተሞክሯል።

በዚህም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የንግዱ ማኅበረሰብ፣ ዲያስፖራው እና የከተማው ነዋሪዎች በገንዘባቸው፣ በእውቀታቸው እና በጉልበታቸው በመልሶ ማለቱ ስራ በከፍተኛ ሁኔታ ተሳትፈዋል። በመንግስት ደረጃም ከባህል፣ ቅርስና ቱሪዝም ቢሮ በተጨማሪ በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤቶች በባለቤትነት ተሳትፈዋል። ይህ ሲሆን ልዩ ካፒታል በጀት አልተመደበም። የመልሶ ማልማቱ ተግባር በሴክተሮች መደበኛ ወጭ እና በህብረተሰቡ ተሳትፎ ብቻ የተከናወነ ነው።

ከመልሶ ማልማቱ ወይም እድሳቱ በፊት ጀጎል እና ዙሪያው ላይ እንኳንስ ለመኖር ለማለፍ የሚከብዱ ቦታዎች ነበሩ። በአሁኑ ግን የአረጋውያን መቀመጫ፤ የህጻናት መጫዎቻ እንዲሆኑ እና ህብረተሰቡም ደስ ብሎት የሚኖርበት ስፍራ እንዲሆን የማድረግ ስራ ተሰርቷል። እድሳቱን በምናከናውንበት ወቅት ቅርሱ ሳይጎዳ፤ ቅድመ ይዘታውን ሳይለቅ ውብ እና ማራኪ እንዲሁም ምቹ የማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል። በእድሳቱ ወቅት የቅርሱ መግለጫ የሆኑ ስዕሎችን ተጠቅመናል።

**አዲስ ዘመን ፡- ሐረር ጥንታዊ ከተማ እንደመሆኗ ከጀጎል በተጨማሪ ሌሎች ቅርሶችን በውስጧ ይዛለች። እነዚህን ቅርሶች በማደስ ለትውልድ ከማስተላፍ አኳያ ምን ሰርታችኋል?**

**አቶ ተወለዳ፡-** ከጀጎል ውጭ ያሉ ቅርሶች ተጠብቀው እና በተገቢው መልኩ ተሰንደው ለትውልድ ለማስተላለፍ አኳያ በርካታ ተግባራትን ስናከናውን ቆይተናል። ጀጎልን ከማደስ በተጨማሪ በክልሉ ‹‹የማንስክሪፕት›› ሙዚዬም እንዲከፈት ተደርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ ሐረር ‹‹በአለላ ስፌትም›› የምትታወቅ ሲሆን በኢትዮጵያ የአዕምሮ ፈጠራ ባለስልጣን እውቅና አግኝተናል። ይህ እውቅናም ‹‹በአለላ ስፌት›› ሐረር በዓለም ገበያ ላይ ተሳታፊ መሆን እንድትችል አድርጓል። ይህን የሐረር መታወቂያ የምናሳይበት የአለላ ስፌት ሙዚዬም ከፍተናል።

ከዚህ ባሻገር በክልሉ ያሉንን ቀደምት ሙዚዬሞች የመንከባከብ፣ የማደስ እና ለቱሪስት ምቹ የማድረግ ስራዎችም በሰፊው ሰርተናል። በዚህም ‹‹የሸሪፍ ሙዚዬምን›› በማደስ ብሔራዊ ሙዚዬም እንዲኖረን ተደርጓል። በፌዴራል ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ለመጀመሪያ ጊዜ ደረጃ በሚሰጥበት ጊዜ አራት ሙዚየሞቻችን እውቅና እንዲያገኙ ማድረግ ችለናል።

ከሐረር ከተማ በተወሰኑ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ በሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ላይ የሚገኙ ቅርሶችን ለማደስ ችለናል። በዚህም ከአንድ ሺህ ዓመት በላይ የሆነው ‹‹የአውብርኸሌ›› አድባር ወይም ‹‹አዎቻ›› ከቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን በተገኘ ድጋፍ እንዲታደስ ተደርጓል። በአሁኑ ጊዜ የመጀመሪያ ምዕራፍ እድሳቱ እየተጠናቀቀ ነው። ‹‹አውጀላን›› የሚባል አካባቢ የሚገኙ ቅርሶችን የማደስ ስራ ተከናውኗል።

በተጨማሪም በሐረር ታዋቂ ግለሰቦች ይኖሩባቸው የነበሩ ቤቶችን በማደስ ሙዚዬም አድርገናል። ከዚህ አንጻር የቀዳማዊ ኃለስላሴ ባለቤት እቴጌ መነን የጫጉላ ቤት እና የቃዲዎኒስ ቤት ተጠቃሽ ናቸው ።

ከዚህም በተጨማሪ ሐረር በሰላም፣ በመቻቻል፣ በአብሮነትና በአንድነት እንዲሁም በመፈቃቀርና በመፈቃቀድ የመኖር እሴት መታወቂያዋ ነው። የተለያዩ ኃይማኖቶች ተከባብረውና ተቻችለው በጋራ የሚኖሩበት ከተማ ናት። ይህንን እሴት ይዞ ለማስቀጠል በየጊዜው የሚፈጠሩ ሳንካዎችን በመቀልበስ አላስፈላጊ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለማድረግ ሰፋፊ ስራዎች ተሰርቷል። በተለይም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱና ወንድማማችነቱ ጸንቶ እንዲቆይ ለማድረግ ቀድሞ የነበረንን እሴት ለማጎልበት በተለይም በጳጉሜ ወር ላይ የሚከበሩ በዓሎችን በሚገባ ተጠቅመንባቸዋል። የአንድነት፣ የአብሮነት ቀን ስናከብር አንዱ የሌላውን እሴት አውቆ፣ አክብሮና ወዶ እንዲኖር የሚያስችሉ ስራዎችን ሰርተናል።

**አዲስ ዘመን ፡- ከሕዝቡ የዘመናዊነት እሳቤ አንጻር የጀጎል ቤቶችን እንዴት አጣጥሞ ማደስ ተቻለ?**

**አቶ ተወለዳ፡-** የሐረር ጀጎል ሲባል ግንቧ ብቻ ሳይሆን በግንቡ ውስጥ የሚገኙ ከ2 ሺህ በላይ መኖሪያ ቤቶችን ይጨምራል። እነዚህ ቤቶች በቅርስነት የተመዘገቡ ናቸው። ይህም ቅርሱን ለማደስ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ያከብደዋል። በጀጎል ውስጥ በየቀኑ ማህኀበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮች ይከናወኑበታል። ይህ ማለት ጀጎልን እየኖርንበት የምንጠብቀው ቅርስ ነው። ከአንድ ሺህ ዓመት በፊት የነበረው እና አሁን ያለው የሰው ልጅ ፍላጎት አንድ አይደለም። የሰው ልጅ እንደየዘመኑ መሰልጠን እና መዘመን ይፈልጋል። ስለሆነም አሁን ላይ ቅርሱን በምናደስበት ወቅት የነዋሪዎችን የመሰልጠን ፍላጎት እና ቅርሱን ይዘት የመጠበቅ ፍላጎትን ሚዛናዊ አድርጎ መሄድ ያስፈልግ ስለነበር ይህን ፍላጎት ለማጣጣም ከፍተኛ ስራዎች ተከናውነዋል።

እውነት ለመናገር ቅርሱን የመጠበቅ እና የሕዝቡን የመዘመን ፍላጎት አጣጥሞ ይዞ መሄድ ትልቅ ፈተና ነው። ከዚህ አንጻር ልምድ እንውሰድ ቢባል በቅርብ ሄደን ልምድ የምንወስድበት ቦታ እንኳን የለም። ኢትዮጵያ ብዙ ቅርሶች አሏት። ነገር ግን እንደ ሐረር ሕዝብ የሚኖርባቸው አይደሉም። በመሆኑም የእድሳት ስራ ሲያከናውኑ እንደ ጀጎል አይቸገሩም። የሐረር ቅርስ ግን ሕዝብ የሚኖርበት በመሆኑ ከአባቶች የተረከብነውን ቅርስ ለማደስ እና አሁን ላይ ሕብረተሰቡ ያለውን የመዘመን ፍላጎት አጣጥሞ ለመሄድ ብዙ ፈተናዎች ገጥመውን ነበር። ይሁን እንጂ ሁሉንም ነገር አጣጥመን በጥበብ ማለፍ ችለናል።

**አዲስ ዘመን፡- በጥበብ ተወጣነው ሲሉ በምን መልኩ ነው?**

**አቶ ተወስዳ፡-** ጀጎል ቅርስ የሆነ ከተማ ስለሆነ ለትውልድ ለማስተላለፍ በምናደርገው ጥረት አንዱ ፈታኝ ነጥብ የግንባታ ቁሳቁስ ማግኘት ነው። የግንባታ ቁሳቁሱን ማግኘት በራሱ ትልቅ ፈተና ነው። ለምሳሌ አንድ የሐረሪ ባህላዊ ቤት ለማደስ ከ500 እስከ 700 ሺ ብር ይፈልጋል። አንደኛ ጣራው የሚሰራው ከወፍራም ጥድ እንጨት ነው። የጥድ እንጨቱ በከተማው ላይ ስለማይገኝ ከሌላ ቦታ ነው የሚመጣው።

የአንዱ ጥድ ዋጋም ከአንድ ሺ ብር በላይ ነው። ቤቱ የተሰራበት ድንጋይም ይለያል። ለምሳሌ የብሎኬት ቤት በብርድ ጊዜ ይበርዳል በሙቀት ጊዜ ይሞቃል። የሐረሪ ቤት ግን ከተሰራበት ድንጋይ ተፈጥሮ የተነሳ እንደ ብሎኬት ቤት አይደለም። በብርድ ጊዜም ሆነ በሙቀት ጊዜ የቤቱን ሙቀት ይጠብቃል። ቤቶቹ የተገነቡበት ድንጋይ የተለየ ነው። ድንጋዮቹ ኩሮን ከሚባል ቦታ ላይ የሚወጡ ናቸው። ጥንታዊ ቤቶች በአይነታቸው በተለዩ ድንጋዮች የተሰራ በመሆኑ እድሳት ስናከናውንም በራሱ ድንጋይ ነው የምናድሰው። ይህም እድሳቱን ፈታኝ ያደርገዋል። ሆኖም የግንባታ እቃዎቹ ያሉበትን ቦታ በመለየት እና በማምጣት የሐረሪ ሕዝብን ፍላጎት በሚመጥን መልኩ ለመገንባት ችለናል።

**አዲስ ዘመን፡- እድሳቱ ከተከናወነ በኋላ ያለው የቱሪዝም ፍሰት ምን ይመስላል?**

**አቶ ተወለዳ፡-** ከእድሳቱ በፊት የቱሪዝም ፍሰቱ በከፍተኛ ደረጃ ማሽቆልቆል ታይቶበት ነበር። በተጨማሪም ኮቪድ በፈጠረው ስጋት እና ከሰላም ሁኔታዎች አንጻር የቱሪስቱ ፍሰቱን በተለይም የውጭ ቱሪስት ፍሰቱ ቀንሶ ነበር። ነገር ግን እንደሌላው አካባቢ ዜሮ አልሆነም። ለምሳሌ በ2013 ዓ.ም 700 አካባቢ የውጭ ቱሪስት ወደ ክልላችን መጥቷል። አሁን ግን እስከ ከ4000 በላይ ቱሪስቶች ወደ ክልላችን መጥተዋል።

ከሀገር ውስጥ ቱሪስት አንጻር አሁን ላይ 127ሺ በላይ ቱሪስቶች ወደ ክልላችን መጥተዋል። በአንጻራዊነት ክልሉ ሰላም በመሆኑ የቱሪስት ፍሰቱ ጨምሯል። የክልሉ ሰላም ለቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋጾ አድርጓል።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ‹‹ሐረር ላይ አንዱ ለአንዱ ጌጥ ሆኖ በመኖሩ...

ከገጽ 7 የዞረ

ባሳለፍነው የሸዋል ኢድ በዓል ላይም እጅግ ሰፊ በሚባል ሁኔታ ብዙ ሰው ታድሟል። እድገቱም ከመቶ ፐርሰንት በላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ‹‹ማንስክሪፕቶችን‹‹ በማዘመን ‹‹ዲጅታሳይዝ‹‹ የማድረግ ለጥናት እና ምርምር እንዲውሉ በሌሎች ቋንቋዎች ከመተርጎም አንጻር ምን ሰራችሁ?**

**አቶ ተወለዳ፡-** አሁን ላይ ያሉንን ማንስክሪፕቶች ዲጅታላይዝ የማድረግ ተግባራት አከናውነናል። ዲጅታላይዝ ያደረግናቸውን ማንስክሪብቶች ለጥናት እና ምርምር የሚውሉበትን መንገድ ለማመቻቸት የተለያዩ ስራዎች ተከናውነዋል። ነገር ግን በተለያዩ ቋንቋዎች ከመተርጎም አንጻር ገና ስራዎችን አልጀመርንም።

ማንስክሪፕቶች በተለያዩ ግለሰቦች እጅ ይገኙ ስለነበር መጀመሪያ እንደቢሮ የሰራነው ከተለያዩ ቦታዎች ማንስክሪፕቶችን መሰብሰብ ነበር። ቅርሶች በተለያዩ ሰዎች እና ቦታዎች ተበታትነው ስለነበር እነሱን የማሰባሰቡን ስራው ገና አልጨረስንም። ሰብስበን ከጨረስን በኋላ የመጠገን፣ የመጠረዝ እና የማስተካከል ስራዎች እንሰራለን። ከዚያ በኋላ ዲጂታላይዝ የማድረግ ስራ ይሰራል። አሁን ላይ ማንስክሪቢቶች በመሰብሰብ እየጠገን እና ዲጅታላይዝ የማድረግ ስራዎችን እየሰራን ነው። በቀጣይነት ለጥናት እና ምርምር እንዲውሉ ለማስቻል የትርጉም ስራ ልናከናውን እንችላለን።

**አዲስ ዘመን፡- በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተጀመረው የጅብ ትርኢት ማሳያ ፕሮጀክት ግንባታ ምን ላይ ደረሰ ?**

**አቶ ተወለዳ፡-** በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመደመር መጽሐፍ ሽያጭ ገቢ የተጀመረው የጅብ ትርኢት ማሳያ ፕሮጀክት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ነው። ለቱሪስቱ ምቹ እንዲሆን በሰጡት አደራ መሰረት የክልላችን ፕሬዚዳንትም አደራውን ተቀብለው የገቢ ማሰባሰቢያ ተደርጓል። በዚህ የገቢ ማሰባሰቢያ ለመጀመሪያ ጊዜ እስከ 70 ሚሊዮን ብር ከሕዝብ መሰብሰብ ተችሏል። በገንዘቡ ዲዛይኑ ተሰርቶ ተጠናቆ ግንባታ ላይ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከ90 በመቶ በላይ ፕሮጀክቱ ተጠናቋል። በቀጣይ አንድ ወር ውስጥ የመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ክፍት ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ሸዋል ኢድን ለሕብረ ብሄራዊ ወንድማማችነት ከመጠቀም አንጻር ምን ተሰርቷል?**

**አቶ ተወለዳ፡-** ሸዋል ኢድን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ ጥረት ሲደረግ ነበር። ይህንንም ከፌዴራል ቅርስ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ቦትስዋና ላይ በተደረገው የማይዳሰሱ ቅርሶች ስብሰባ ላይ ተቀባይነት አግኝቶ ተመዝግቧል።


ሀገራችን የማይዳሰሱ ቅርሶችን በማስመዝገብ ቁጥር በመጨመር ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ቀዳሚ እንድትሆን አድርጓል። በዚህም ሐረር የሚዳሰስና የማይዳሰስ ቅርስ በማስመዝገብ ቀዳሚ ከተማ ያደርጋታል። በእነዚህ ስራዎች በቂ ስራ ተሰርቷል ማለት ይቻላል።

የሸዋል ኢድ በዓልን "ሕብረ ብሄራዊነታችን ለቱሪዝም እድገታችን" በሚል መሪ ቃል ስናከበር ቆይተናል። ወደፊትም በዚህ ልክ ይከበራል። ይህም ወንድማማችነትን እና አብሮነትን አጠናክሮ ለትውልድ እንዲሸጋገር ከማድረግ አኳያ ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በሐረሪ ክልል የተለያዩ ብሔር ብሔር ብሔረሰቦች መገለጫ የሆኑ ሙዚየሞች ተገንብተዋል፤ እየተገነቡ ያሉም አሉ። እነኝህ ሙዚየሞች የሐረርን የሰላም ከተማነት እሴት ከማጉላት አንጻር የሚኖራቸውን ፋይዳ እንዴት ይገልጹታል ?**

**አቶ ተወለዳ፡-** ሙዚዬሞችን እየሰራን ያለው በክልሉ ቱሪዝም ቢሮ ግቢ ውስጥ ነው። መጀመሪያ የሐረሪ ባህላዊ ቤቶች ተሰርተዋል፣ ቀጥሎም የኦሮሞ ባህላዊ ቤቶች እና የአባገዳ እልፍኝ ተሰርቷል። የአባገዳ እልፍኝ ሲሰራ እያንዳንዱን ኦሮሞ ባህልና እሴቶች እንዲሁም ትውፊቱን በጠበቀ መንገድ ነው። ከኦሮሞ የባህል ማዕከል በተጨማሪ የሶማሌና የአፋር ክልሎችም የባህል ሙዚዬሞቻቸውን ለመገንባት በሂደት ላይ ናቸው ።

ይህም የምስራቁ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙ ሕዝቦችን



ቀደም ብሎ የነበራቸውን በሰላም፣ በአብሮነት የመኖር እሴቶቻቸውን የበለጠ አጠናክረው እንዲያስቀጥሉ ትልቅ እገዛ ያደርጋል። ሐረርንም ቀድሞ የነበራትን እሴት ይመልሳል።

**አዲስ ዘመን፡- ሐረር የሰላም ከተማ ተብላ በዩኒስኮ ሽልማት እንድታገኝ ያስቻሳት ምክንያት ምንድነው?**

**አቶ ተወለዳ፡-** ሐረር የሰላም ከተማ በመባል በዩኒስኮ ሽልማት አግኝታለች። ሐረር ላይ የሚገኙ ኃይማኖቶችን ብንወስድ በአንድ ቦታ ላይ ያለምንም ችግር ከ110 ዓመታት በላይ የቆዩ ሶስት ኃይማኖቶች አሉ። እነዚህ ኃይማኖቶች በአንድ ስፍራ ያለምንም ችግር የአምልኮ ተግባራቸውን እያከናወኑ ይገኛሉ። አንዱ ለአንዱም ጌጥ ነው።

በሌላ መልኩም የሕብረተሰቡን አኗኗር ማየት እንችላለን። በአንድ ግቢ ውስጥ የተለያዩ ብሄሮችና ኃይማኖቶች በመቻቻል አንዱ የሌላውን ወዶና አክብሮ የሚኖርባት ከተማ ናት። ሐረር ላይ አጽንተው ያቆዩንም እነዚህ እሴቶቻችን ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ሐረር ላይ ያለው መቻቻልና አብሮነት ለቱሪዝም ዘርፉ እድገት ምን አስተዋጽኦ አለው?**

**አቶ ተወለዳ፡-** ጀጎል ውስጥ በቀደመው ጊዜ የተገነቡ ከ99 በላይ መስጊዶች አሉ። እነዚህ መስጊዶች ግማሾቹ ከ500 ዓመታት በላይ እድሜ ያላቸው ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከ1000 ዓመት በላይ እድሜ ያላቸው ናቸው። እነዚህ መስጊዶች ባሉበት አካባቢ የኦርቶዶክስ እና ካቶሊክ ቤተክርስቲያን አብረው አሉ። በአንድ ግቢ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች መኖር ብዙ ሰው ሊከብደው ይችላል። ነገር ግን ሐረር ላይ ምንም አይነት ልዩነት ሳይፈጠር ልዩ ውበት ነው ብለው እየኖሩ ነው።

የሐረርን አብሮነት ሚስጥር አንዳንድ አካላት እንጠቀምበት ካሉ ለግጭት መንስኤ ሊያደርጉት ይችላሉ። እኛ ግን ይህን ለአብሮነታችን ተምሳሌት አድርገን ይዘን እየቀጠልን ነው። ይህም የሆነው አንዱ የሌላውን ባህልና የሚከተለውን እምነት እያከበረ ስለሚኖር ነው።

በመድሃኒዓለም ቤተክርስቲያን ያሉ አባቶች የመስጊዱን አዛን ይሰማሉ። በዚህም የሚሰሙት የድምጽ ማን እንደሆነ ስለሚያውቁ ድምጹ ብዙ ጊዜ ከጠፋ አዛን የሚያደርገው ሰው የት ሄደ? ብለው ይጠይቃሉ። ይህ በተግባር የሆነ ነው። አንድ የኦርቶዶክስ አባት ለረጅም ጊዜ ሲሰሙት የነበረው አዛን የሚያደርጉ አባት ድምጽ ሲጠፋባቸው ምን ሆነው ነው? ታመው ነው ወይስ አርፈው? ብለው መስጅድ ድረስ ሄደው ጠይቀዋል። ይህ ለማኅበራዊ ትስስሩ ጠንካራ መሆን ትልቅ ማሳያ ነው። ስለሆነም ሐረር ላይ አንዱ ለአንዱ ሸክም ሳይሆን ጌጥ ሆኖ እየኖረ ነው። ይህ ለሌላው የሀገሪቱ ክፍል ምሳሌና ተሞክሮ የሚሆን ነው። ይህም ለቱሪዝም ፍሰቱ ከፍተኛ አስተዋጾ ያለው ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ የሜዲካል ቱሪዝምን ከማስፋፋት አኳያ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ተወለዳ፡-** በሐረር የሚገኘው ጀጉላ ሆስፒታል በእድሜ በኢትዮጵያ ሁለተኛው ነው። አሁን ላይ የጀጉላ ሆስፒታልን ጨምሮ በርካታ ሆስፒታሎች ይገኛሉ። በመሆኑም በሐረር ከአጎራባች ክልሎች የሚመጡ ታካሚዎች በብዛት አገልግሎት ያገኛሉ። ይህም ለሜዲካል ቱሪዝም እድገት የራሱ የሆነ አስተዋጾ አለው። የሜዲካል ቱሪዝም ለማሳደግ እንደክልል የተጀመሩ ስራዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል የጤና ኮርደር ልማቱ ተጠቃሽ ነው። ይህ የኮሊደር ልማት ሲጠናቀቅ የሜዲካል ቱሪዝም ፍሰቱን እንደሚጨምር ይጠበቃል።

**አዲስ ዘመን፡- ለቱሪዝም ፍሰቱ ሆቴሎች ትልቅ ሚና አሳቸው ፤ሐረር ላይ ያንን መሸከም የሚችል የሆቴሎች ጥራት እና ቁጥር አለ? በዚህ ዘርፍስ ኢንቨስተሮች እንዲሳተፉ ምን አይነት ጥረት እያደረጋችሁ ነው?**

**አቶ ተወለዳ፡-** ሐረር ላይ ትልቁ ጉድለታችን ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች አለመኖር ነው። የቱሪስቶች የመቆያን ጊዜ እያሳጠረው ያለው ይሄው ችግር ነው። ይሄንን ችግርም ለመቅረፍ በሁለት መንገድ እየተሰራ ነው። የመጀመሪያው ያሉት ሆቴሎች ብቃትና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ነው። ከዚህ አኳያ ሆቴሎች ያሉባቸውን ክፍተቶች በማጥናት በስልጠና፣ በክትትልና በቁጥጥር እንዲስተካከሉ የማድረግ ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን።

ሁለተኛ የሆቴል ክፍተቱን ለመሙላት ለኢንቨስትመንት ቦታ ያዘጋጀንበት ሁኔታ አለ። ትልልቅና ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች እንዲገነቡ ቦታ ተዘጋጅቷል። በቅርቡ ክልሉ ጥሪ በማድረግ ኢንቨስተሮችን ይጋብዛል።

በዚህ አጋጣሚ በሐረር ከተማ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች ለመገንባት ፍላጎት ያላቸውን ኢንቨስተሮች ሐረር ለማስተናገድ ዝግጁ ናት። በኢኮ ፓርኩ እና በከተማው የተለያዩ ቦታዎች ላይ የተዘጋጁ ቦታዎች አሉ። አሁን ላይ እየተገነቡ ያሉ ሆቴሎችም አሉ። የእነዚያን ግንባታዎች እያበረታታን እንገኛለን። የቱሪስቶች የቆይታ ግዜ ለመጨመርም እየሰራን እገኛለን።

ኢኮ ፓርኩ ሲጠናቀቅም የቱሪስቶችን ቆይታ ያራዝማል። በቀን እና በምሽት አገልግሎት ይሰጣል፤ የጅብ ትርኢቱን ማሳየት ይችላል። ከዚህም ቱሪስቱን በመሳብ ሐረር ላይ እንዲቆይ የሚያስችሉ ስራዎችን በስፋት እየተከናወኑ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- አስጎብኚዎችን በማስተማርና በማሰልጠን ረገድ ምን እየሰራችሁ ነው?የቱሪዝም ዘርፉ ስራ ዕድልን ከመፍጠር አኳያ ምን እያበረከተ ነው ?**

**አቶ ተወለዳ፡-** ከኢትዮጵያ አስጎብኚዎች ማህበር ጋር ትስስር ፈጥረን እየሰራን ነው። ከ35 በላይ ለሚሆኑ አስጎቢኚዎቻችን ስልጠና እንዲወስዱ አድርገናል። ሰልጣኞቹ እራሳቸው አምባሳደር እንደሆኑ አውቀው የገጽታ ግንባታ ስራ እንዲያከናውኑ ተደርጓል።

በቀጣይ ከሌላ አካባቢ ካሉ አስጎብኚዎች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩና አካባቢያቸው ላይ ያለውን ቱሪስት ወደዚህ እንዲልኩ፤ እዚህ ያለውንም ወደዛ እንዲጋብዙ ለማድረግ እየሰራን ነው። ከድሬደዋ፤ ከሱማሌ ጋር አብረን መስራት የምንችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት እያደረግን ነው። በዋናነት ግን በዚህ ዓመት የሰራነው ስልጠና መስጠትና ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር እንዲተዋወቁ የማድረግ ስራዎችን ነው። በዚህም ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ ያሉትን የቱሪስት ሀብቶች ለማስተዋወቅ ደረጃቸውን የጠበቁ ማስተዋወቂያዎችን ከመስራትና ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ምን ሰርታችኋል?**

**አቶ ተወለዳ፡-** በቅርቡ ወደ ትግበራ የገባ ‹‹ቪዚት ሐረር›› የሚል የዌብሳይ ፔጅ አለን። ቪዚት ሐረር ፌስቡክ እና በሌሎች የማህኅበራዊ ድረገጾች የማስገባት ስራዎችን እሰራን ነው ። በዚህም አንድ ቱሪስት መነሻ ቦታው ላይ ሆኖ ሐረርን ማየት የሚችልበትና ከሆቴሎች ጋርም ትስስር መፍጠር የሚችል መተግበሪያ ነው። በዚህ መተግበሪያ ማንኛውም ሰው በስልኩ ስለ ሐረር ማወቅ ይችላል። ይሄ ግን በቂ አይደለም።

የማስታወቂያዎች ወጪ ውድ ነው። ጥራታቸው ሲጨምር እና ትልልቅ ሚዲያዎች ላይ እናስተዋውቅ ሲባል ዋጋቸው ይጨምራል። ነገር ግን በራሳችን አቅምና ባለሙያ የሚሰሩት ላይ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወንን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከሌሎች ክልሎች ጋር ያሳችሁ የልምድ ልውውጥ ምን ይመስላል?**

**አቶ ተወለዳ፡-** የልምድ ልውውጥ ለማድረግ አንድ መድረክ አዘጋጅተን ነበር። ይህም በአምስቱ አጎራባች ክልሎች ካሉ የቱሪዝም ቢሮዎች ጋር በመተባበር የሚሰራ ነበር። ዋና ሃሳቡም ድሬደዋን፣ ኦሮሚያን፣ አፋር እና ሱማሊያን ለመጎብኘት የመጣ ቱሪስት ሐረርን ሳይጎበኝ መሄድ የለበትም የሚል ነው። ሐረርን ሊጎበኝ የመጣ ጎብኝም በተመሳሳይ ሌሎችን ቦታዎች እንዲጎበኝ ለማድረግ የተዘጋጀ ክላስተር ነበር። ተባብረን ተሳስረን መሄድ አለብን የሚል ተነሳሽት ነው። ያንን አጠናክረን እንሄዳለን። ከሁሉም ክልሎች ጋር የመግባቢያ ሰነዶችን ተፈራርመናል። ግን ያንን ወደ ስራ ማስገባት ይቀረናል፤ በሰፊው መስራት አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን።**

**አቶ ተወለዳ፡-** እኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# አዳዲስ የኢንቨስትመንት እድሎችን የሚፈጥረው ‹‹ገዳ›› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን

**አንተነህ ቸሬ**

ሀገራት የኢንቨስትመንት ዘርፋቸውን በማሳደግ ጥቅል አገራዊ እድገታቸውን ዘላቂ ለማድረግ ከሚተገብሯቸው አሰራሮች መካከል አንዱ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን (Special Economic Zones) ማቋቋም ነው። ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች የሚፈጥሩትን የስራ እድል፤ ለአገር በቀል የሎጂስቲክስ ኢንዱስትሪው መስፋፋት የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርንና የባለሙያዎችንና የሠራተኞችን ክህሎት ለማሳደግ እና የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ የሚኖራቸውን ወሳኝ ሚና እንዲሁም የወጪና ገቢ ንግድን ለማቀላጠፍ ያላቸውን አበርክቶ በአጠቃላይ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት መሻሻል የሚኖራቸውን ጉልህ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት አገራት ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን ያቋቁማሉ፣ ያስፋፋሉ።

የምጣኔ ሃብት ሳይንስ ጥናቶች እንደሚያስረዱት፤ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ኢንቨስትመንትን በማሳደግ ለስራ እድል ፈጠራ፣ ለምርት አቅርቦት እና ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ። የእነዚህ ቀጣናዎች ዋና ዋና ዓላማዎች የስራ እድል ፈጠራን እና ምርትንና ምርታማነትን መጨመር፣ የወጪ ንግድን ማስፋትና የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ እንዲሁም ካፒታልና ቴክኖሎጂን መሳብ ናቸው። ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች የራሳቸው የምርት ስፍራ/ወሰን፣ የአስተዳደር ስርዓት፣ የታክስ ሕግጋት እና የጉምሩክ ስርዓት አላቸው። ቀጣናዎቹ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ፣ በጥሬ እቃ አቅርቦት እንዲሁም በምርት አቅርቦትና ግብይት ተግባራት ላይ የሚሰማሩ አካላትን ቁጥር ይጨምራሉ። ይህም የልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ልማት ከኢንቨስትመንት እድገት ጋር ቀጥተኛ ትስስር እንዳለው ማሳያ ነው።

ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች የግል (Private) እና የመንግሥት (Public) ኢንቨስትመንቶችን በማበረታታት የኢንቨስትመንት ዘርፉ እንዲያድግ ያስችላሉ። ቀጣናዎቹ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን (Foreign Direct Investment) በመሳብ የግል ባለሃብቶች በስፋት በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ያደርጋሉ። በሌላ በኩል ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ሰፊ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎችን የሚፈልጉ በመሆናቸው መንግሥት በመሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት (Infrastructural Investment) ላይ እንዲሰማራ በማድረግ የመንግሥት ኢንቨስትመንት እንዲነቃቃ እድል ይፈጥራሉ። በአጠቃላይ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ለባለሃብቶች ምቹ እድሎችን የሚፈጥሩ በመሆናቸው ባለሃብቶች በኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ተነሳሽነት ይኖራቸዋል።

በልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ውስጥ የሚተገበሩ ሕጋዊ አሰራሮች ቀለል ያሉና ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን የሚቀንሱ በመሆናቸው ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ለመሰማራት የሚያደርጉትን ጥረት በአንፃራዊነት ቀላል ያደርጉላቸዋል። በነፃ የንግድ ቀጣናው ውስጥ ገብተው የሚሠሩ ባለሀብቶች፣ አስመጪና ላኪዎችም ሆኑ ድርጅቶች የልዩ ልዩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር እንዲሁም መሬትን ጨምሮ ሌሎች እምቅ ሀብቶች ያላት ኢትዮጵያ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን በማቋቋም ረገድ በመዘግየቷ ከእነዚህ ቀጣናዎች ልማት ማግኘት የሚገባትን ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅም ማጣቷ ተደጋግሞ ሲገለፅ ቆይቷል። የሀገሪቱን የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ እግር ከወርች አስረው የያዙት አንዳንዶቹ መሰናክሎች ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች በሚያስገኟቸው ጥቅሞች የሚፈቱ ናቸው። ስለሆነም ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን በማቋቋም የሀገሪቱን ተጠቃሚነት ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ለማልማት የሚያስችሉ ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል።

የልዩ ኢኮኖሚ ቀጣናዎች ልማት በሕጋዊ ማዕቀፍ የተደገፈ እንዲሆን የሚያስችሉ ብሔራዊ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ፖሊሲ እና የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ (1322/2016) ተዘጋጅተው ወደ ስራ ተገብቷል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ነሐሴ 27 ቀን 2014 ዓ.ም ባካሄደው 11ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ በብሄራዊ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ረቀቂ ፖሊሲ ሰነድ ላይ ውይይት በማድረግ፣ ፖሊሲው በሥራ ላይ እንዲውል በሙሉ ድምጽ ወስኗል። ምክር ቤቱ ፖሊሲው በስራ ላይ እንዲውል ውሳኔ ያሳለፈው ኢትዮጵያ ለአገራዊ የኢኮኖሚ እድገት የጎላ አስተዋፅዖ ባለውና ከጊዜ ወደ ጊዜ በፍጥነት እየተስፋፋና እየጎለበተ በመጣው ዓለም አቀፍ እና ቀጣናዊ የንግድ ትስስር ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንድትሆን አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

ፖሊሲው የአገሪቱን የወጪ ንግድ ስርዓት ለማሻሻል፣ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ስበትን ለማሳደግ፣ የወጪ ንግድ አቅምን ለማጎልበት፣ ሰፊ የስራ እድሎችን ለመፍጠር እንዲሁም በአገሪቱ ዋና ዋና የንግድ ኮሪደሮች የደረቅ ወደቦችን ለማስፋፋትና የሎጂስቲክ አገልግሎትን ለማቀላጠፍ የሚያግዙ ስርዓቶችን እውን ለማድረግ የሚያስችል እንደሆነም ተገልጿል።

ከዚህ በተጨማሪም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው ሦስተኛ ዓመት የሥራ ዘመን 21ኛ መደበኛ ስብሰባው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅን አፅድቋል። የውጭ ኢንቨስትመንትን በቀላሉ ለመሳብ፣ ሰፊ የስራ ዕድል ለመፍጠር፣ የአምራች ዘርፉን ለማበረታታት፣ የምጣኔ ሀብት ትስስርን ለማጠናከር፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማሳለጥ እንዲሁም ተግባራዊ የተደረገውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ስርዓት ዲዛይንና ትግበራ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስርዓት በማሳደግ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ተገልጿል።

ነሐሴ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ተመርቆ ስራ የጀመረው የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና (Dire Dawa Free Trade Zone)፣ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገነባው ‹‹አዲስ ቱሞሮው›› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን እና ግንባታው በኦሮሚያ ክልል የሚከናወነው ‹‹ገዳ›› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑት የልዩ ኢኮኖሚ ቀጣናዎች ግንባታ አካል ናቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ግንቦት ሁለት ቀን 2016 ዓ.ም ግንባታውን ያስጀመሩት ‹‹ገዳ›› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በግዙፍነቱም ሆነ በአዋጭነቱ ከሌሎቹ የላቀ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ነው። ልዩ የኢኮኖሚ ዞኑ በ24ሺ ሄክታር መሬት ላይ የሚገነባና በአራት ምዕራፎች የሚለማ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ በ3114 ሄክታር መሬት ላይ ለመጀመር አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል። ‹‹ገዳ›› ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ለኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችለውን የአልሚነት ስምምነት ሰሞኑን ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር ተፈራርሟል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ዶክተር ዘለቀ ተመስገን፣ የገዳ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ትልቅ ሚና እንዳለው ይገልፃሉ። እሳቸው እንደሚሉት፣ የልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ወደ ትግበራ መግባት መቻል የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማጎልበትና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ወደ ኢትዮጵያ ለመሳብ በሚደረገው ጥረት ውስጥ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። ለኢንዱስትሪያላይዜሽን መስፋፋት፣ ለቴክኖሎጂና ለእውቀትና ሽግግር እንዲሁም ለስራ እድል ፈጠራ አጋዥ ይሆናል። ለሀገር ውስጥና ለውጭ ባለሃብቶች አዳዲስ የኢንቨስትመንት እድሎችን ይፈጥራል። ኢትዮጵያም በቀጣናውም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለኢንቨስትመንት ይበልጥ ተፈላጊና ምቹ ሀገር ሆና እንድትቀጥል ትልቅ አስተዋፅዖ ያደርጋል።

‹‹በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንና በገዳ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን መካከል የተፈረመውን የአልሚነት ስምምነት ተከትሎ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኑ ለንዑስ አልሚዎች፣ ለድርጅቶች፣ በአጠቃላይ ለባለሃብቱ ምቹ መደላድል መፍጠር ይጠበቅበታል። በተለይም ለባለሃብቶች አስፈላጊ መሰረተ ልማቶችን ማሟላት፣ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር በመሆን ሌሎች አገልግሎቶች በተገቢ ሁኔታ እንዲሟሉ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ከማደራጀት ጀምሮ በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጁ ላይ የተቀመጡትን ሌሎች ድጋፎችን ለገዳ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን የሚያደርግ ይሆናል። የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ለማሸጋገር አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት ላይ ይገኛል›› ይላሉ።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንዲጠናከር የውጭ ባለሃብቶችን በመሳብና በመመልመል፣ የተመለመሉትን ወደ ተግባር በማሸጋገር፣ ወደ ተግባር ለተሸጋገሩት ደግሞ ጠንካራ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሃብት እድገት ጉልህ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሚገኝ የሚናገሩት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ የ‹‹ገዳ›› ልዩ የኢኮኖሚ ዞን መቋቋምም የዚሁ ማሳያ እንደሆነ ያስረዳሉ።

የ‹‹ገዳ›› ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሞቱማ ተመስገን በበኩላቸው፣ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኑ በአፍሪካ ትልቅ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን የመገንባት ራዕይ ያለው የምጣኔ ሀብት ቀጣና እንደሆነ ይገልፃሉ። ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚያስረዱት፣ ተልዕኮውም መሰረተ ልማቶችን በማቅረብና ኢንቨስተሮችን በመቀበል፣ ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆነ ዞን ማዕከልን መገንባትን ማዕከል ያደረገ ነው። የስራ እድሎችን የመፍጠር፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን የመሳብ፣ የውጭ ምንዛሬ የማስገኘትና የምጣኔ ሀብት እድገትን የማፋጠን ዓላማዎች ያሉት ልዩ የኢኮኖሚ ዞኑ፣ በ24ሺ ሄክታር መሬት ላይ የተቋቋመና በአራት ምዕራፎች የሚለማ ይሆናል።

‹‹የኢኮኖሚ ዞኑን ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ባለብዙ ዘርፍ ዞን መሆኑ ነው። በውስጡ ለኢንዱስትሪ ብቻ የሚሆን 5000 ሄክታር መሬት አለው። የገበያ ፈጠራን መሰረት ያደረገ፣ ሰፊ መሬት ላይ ያረፈ፣ በከፍተኛ የአዋጭነት ጥናት ላይ የተመሰረተ፣ ብዙ መሰረተ ልማቶች ባሉበት አካባቢ የሚገነባ (ፈጣን መንገዶች የሚገናኙበት፣ የሀገሪቱ የሎጂስቲክስ ማዕከል በሚባለው ከሞጆ ደረቅ ወደብ አካባቢ የሚገኝ፣ ከባቡር መስመር ጋር የተገናኘ) የኢኮኖሚ ማዕከል ነው›› ይላሉ።

እንደ አቶ ሞቱማ ገለፃ፣ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር የተደረገው የአልሚነት ስምምነት ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን እንዲጠቀሙ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲቋቋም እንዲሁም የግብይትና የፕሮሞሽን ስራዎችን በጋራ ለመስራት የሚያስችል ነው።

ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ከሚሰጠው ከልዩ የኢኮኖሚ ቀጣና ስርዓት ርቃ መቆየቷ ብዙ ጥቅሞችን አሳጥቷታል። የእነዚህ ጥቅሞችና እድሎች መታጣት ደግሞ በአጠቃላይ አገራዊ እድገቷ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረባት አይካድም። ስለሆነም ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን ለማቋቋም የተጀመሩትን ጥረቶች በማጠናከር አገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገቱ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያስመዘግብ ማድረግ ይገባል።

**የልዩ ኢኮኖሚ ዞኑ ወደ ትግበራ መግባት መቻል የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማጎልበትና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ወደ ኢትዮጵያ ለመሳብ በሚደረገው ጥረት ውስጥ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል**

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# በራስ ወርቅ መድመቅ

**ስምስም መንግሥቱ**

ወይዘሮ ፋጤ ሰሞኑን የጤና ችግር አጋጥሟቸው ተኝተዋል። በጤናቸው ምክንያትም ጎረቤታቸው ወይዘሮ ይመናሹም ቤት ቡና ከጠጡ ቀናቶች ተቆጥረዋል። ቡና መጠራራቱ ቀረ እንጂ ጎረቤታቸው ወይዘሮ ይመናሹ ከወይዘሮ ፋጤ ቤት አልጠፉም። አጥሚቱንም ገፎውንም እያደረጉ ጠዋት ማታ ይጠይቋቸዋል። እያስታመሟቸው ነው።

ቡናም እዛው ቤታቸው አፍልተው አብረው ይጠጣሉ። ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ ማታ በመኝታ ሰአት ብቻ ነው የሚለያዩት። በጉርብትና ረጅም ዓመት አብረው በመኖራቸው አብሮነታቸው በጣም የጠነከረ ነው። እንደታላቅና ታናሽ እህት ነው የሚተያዩት። አንዳቸው የጤና ችግር ሲያጋጥማቸው ሌላዋ ያስታምማሉ። ይረዳዳሉ።

የሁለቱን ጎረቤታሞች መተሳሰብና መዋደድ የሚያዩ የአካባቢያቸው ነዋሪዎችም ‹‹ጉርብትና እንደነሱ ነው›› ይላሉ። አንዳንዶችም መንፈሳዊ ቅናት ያድርባቸዋል። የወይዘሮ ፋጤና የወይዘሮ ይመናሹ መተሳሰብ ‹‹ከዓይን ያውጣችሁ›› የሚባለው አይነት ነው።

ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ ከግማሽ በላይ እድሜያቸውን አብረው ነው ያሳለፉት። በመካከላቸው አለመግባባት ሳይፈጠር ቀርቶ አይደለም። ግን የከረረ ነገር አልገጠማቸውም። ተጣልተው ለማስታረቅ ሽማግሌ በመካከላቸው ገብቶ አያውቅም። ነገሮችን ቀለል አድርጎ በማየትና ሆደ ሰፊም ሆኖ በማሳለፍ ጭምር ነው አብሮነታቸውን ያጠናከሩት።

በጉርብትና፣ በጓደኝነት፣ በትዳር አጋሮች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በሀገራችን ባህልና ወግ የችግሮች መፍቻ መንገዱ ሽምግልና ነው። በአካባቢ ማህበረሰብ ከበሬታ ያላቸው፣ በሥነምግባራቸው ጥሩ የሚባሉና ሀቀኛ ተብለው የሚታወቁ ሰዎች ተመርጠው ያልተግባቡ ወይንም የተጣሉ ሰዎችን እንዲሸመግሉ ይደረጋል። በዳይና ተበዳይም ቢሆኑ ሽማግሌዎችን ያከብራሉ። በፊታቸው ቀርበው ችግሮቻቸውን ያስረዳሉ። ሽማግሌዎቹም ከወገኝተኝነት ነፃ ሆነው በሁለቱም ወገን ያለውን ችግር ጠይቀው ጉዳዩን መርምረው ችግሩ በእርቅ እንዲፈታ ያደርጋሉ። በዳይ ተበዳይን እንዲክስም ይወስናሉ።

በዚህ መልኩ አለመግባባቱ ከተፈታ በኋላም ተጣልተው የነበሩ ሰዎች ወደቀደመው ችግር አይመለሱም። ተስማምተው ሰላማዊ ኑሮአቸውን ይመራሉ። በዚህ ወቅት ወይንም በዚያኛው ጊዜ ለማለት ቢያስቸግርም አሁን ላይ በሰዎች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር መፍትሄ ለመስጠት ጥረት ከማድረግ ይልቅ ነገሩን አክርሮ አላስፈላጊ ወደሆነ ፀብና መጎዳዳት ላይ ሲደርሱ ይስተዋላል። እንዲህ ያለው ሁኔታ ከቀጠለ ደግሞ ዋጋ ያስከፍላል።

ሰዎች በመነጋገር አለያም በሽማግሌ ችግሮቻቸውን ፈተው ተስማምተው አብረው መኖር እየቻሉ ቂምና ቁርሾ ይዘው የከረረ ነገር ውስጥ ይገባሉ። ይህ በመሆኑ የተጠቀመ ሰው የለም። ይልቁንም ለጤና እና ለተለያየ ችግር ነው የሚጋለጡት።

እንደው ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ በጉርብትና ሲኖሩ ከግጭት ይልቅ አብሮነትን ማስቀደማቸው ለሌሎች ምሳሌ ይሆናል ብለን ጉዳዩን እንዲህ አነሳን እንጂ ወይዘሮ ይመናሹና ፋጤ አብረው ሲውሉ የሚያወጉት ወግም ጊዜ ማሳለፊያ ብቻ አይደለም። ሌሎችንም ያስተምራል።

በተለይ ደግሞ የሚያነሷቸው ነጥቦች ይሄንንም ይታዘባሉ ማለት ነው? ብለው እጅዎን በአፍዎ ላይ አድርገው እንዲገረሙ የሚያደርጉ ናቸው። ጎረቤታሞቹ የተማሩ አይደሉም። የቢሮ ሠራተኛም አይደሉም። በአነስተኛ ንግድ ሥራ ነው ኑሮአቸውን ሲመሩ ነው የኖሩት። ግን በተፈጥሮ አስተዋይ ናቸው። በነገሮች ላይም መወያየትን መጠያየቅን የሚወዱ ናቸው። አንዳቸው የሰሙትን ነገር ለሌላኛቸው የመንገር ባህልን አዳብረዋል። ንቁ እንዲሆኑ ያደረጋቸውም ይኸው ተሞክሮአቸው ነው።

ምንም እንኳን ወይዘሮ ፋጤ ታመው አልጋ ላይ ቢሆኑም ወይዘሮ ይመናሹ ከቤታቸው ስለማይጠፉ በየቤታቸው ቡና እየተጠራሩ እንደሚጫወቱት ሁሉ ወይዘሮ ይመናሹ ወይዘሮ ፋጤ ቤት በመሄድ ይጫወታሉ። ደግሞ ጨዋታ በሽታ ያስረሳል ይባል የለ? ወይዘሮ ይመናሹም የተለያዩ ርእሰጉዳዮችን እያነሱ ለማጫወት ሙከራ ያደርጋሉ። ወይዘሮ ፋጤም ቢሆኑ ለጎረቤታቸው ምላሽ ለመስጠት አልቦዘኑም። የሚሰማቸውን ሃሳብ ይሰነዝራሉ።

በጨዋታቸው ጊዜ ወስደው ያነሱት ጉዳይ የባህልና ወግ መበረዝና እየተሸረሸረ መሄድ ነው። የኢትዮጵያ መገለጫ የሆኑ አንዳንድ ባህልና ወግ እሴቶች እየተሸረሸረ ሄዷል ብለው ያምናሉ። ባህሉ ተሸርሽራል ብለው ካነሷቸው ጉዳዮች አንዱ አሁን ላይ እየተስተዋለ ያለውን የሽምግልና ሥርዓት ጉዳይና የወፍ አጥር አትይሽ ተብሎ ለመውለድ ቀኗ ለተቃረበ ሴት እየተደረገ ስላለው ዝግጅት ነው።

ያነሱት ርእስጉዳይ ብዙ ሲያከራክራቸው ነበር። እነርሱ ያለፉበትና አሁን ላይ የሚያስተውሉት ፈጽሞ ስለተራራቀባቸው የትኛው ዘመን ይሻላል የሚለው መደምደሚያ ላይ ለመድረስ እንኳን አልቻሉም። ግን ደግሞ የራስ የሆነ የባህል፣ የታሪክ፣ የሥነምግባር፣ ሌሎችም መገለጫዎች፣ እሴቶች ሊኖሩ ይገባል ብለው ያምናሉ።

ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ የዘመኑን ቴክኖሎጂ ባይጠቀሙም ከልጆቻቸው፣ ከጎረቤት ልጆችም የማየቱን ዕድል ስለሚያገኙ እየሆነ ያለውን ታዝበዋል። ዛሬ በተንቀሳቃሽ የእጅ ስልካችን እየተለቀቀ የምናየውን ልጅህን ለልጄ ተብሎ ለሚላከው ሽምግልና እና ለመውለድ ለተቃረበች ሴት የወፍ አጥር አትይሽ ተብሎ የሚዘጋጀውን ድል ያለ ድግስና ጭፈራ ነው ጎረቤታሞቹን አግራሞት የጫረባቸውና በጉዳዩ ላይም ለመነጋገር ያነሳሳቸው።

በርእሰ ጉዳዩ ላይ ጨዋታውን የጀመሩት ወይዘሮ ይመናሹ ነበሩ። እርሳቸው ሲዳሩ የነበረውን ሁኔታ ወደኋላ መለስ ብለው ዘመኑን እንዲህ አስታወሱ፤ የልጆቻቸውን አባት ሲያገቡ የሚያውቋቸው ሰው ሊሆኑ ቀርቶ የሚያስቧቸው እንኳን አልነበሩም። እርሳቸው ባገቡበት ዘመን ልጅህን ለልጄ ብለው ለልጆቻቸው የትዳር አጋር የሚመርጡት ወላጆች ናቸው የነበሩት።

ሽማግሌም ሲላክ ሙሽሪትና ሙሽራው አያውቁም። ወላጆች በሚያደርጉት ስምምነት የሰርጋቸው ቀን ተቆርጦ ለሰርግ ዝግጅት ሲደርግ ነው ተጋቢዎቹ እንዲያውቁ የሚደረገው። አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ልጆች ጋብቻውን አይቃወሙም። የቤተሰብ ትእዛዝ ይከበራል። ከወላጆቻቸው ፈቃድ አይወጡም።

ወይዘሮ ይመናሹ እንዳሉት፤ ሽምግልና በጣም ከባድ ነው። ወላጆች በቀላሉ ስለማይቀበሏቸው ሽማግሌዎች ከብዙ መመላለስ በኋላ ነው መልስ የሚያገኙት። ሽማግሌዎቹ ተመላልሰው፣ ደክመው እንኳን መልሱ አይሆንም የሚልም ሊሆን ይችላል። ከቻሉ ያሳምናሉ። ካልተሳካላቸውም በፀጋ ከመቀበል ውጭ አማራጭ የላቸውም። ወይዘሮ ይመናሹም በወቅቱ በነበረው ባህልና ወግ ነው የአሁኑን የልጆቻቸውን አባት በሰርግ ያገቡት።

ወይዘሮ ይመናሹ በእሳቸው ጊዜ የነበረውን የሽምግልና ሥርዓት ትክክል እንደሆነ አድርገው ይቀበላሉ። ለታይታ ሳይሆን፣ ለሚጋቡትም የሚጠቅም ነው ብለው ያምናሉ። ተጋቢዎቹ ችግር እንኳን ቢያጋጥማቸው ችግራቸውን በቤተሰብ

**ነገሮችን ቀለል አድርጎ በማየትና ሆደ ሰፊም ሆኖ በማሳለፍ ጭምር ነው አብሮነታቸውን ያጠናከሩት**

ዙርያ ለመፍታት ዕድል ያገኛሉ የሚል እምነት አላቸው።

ስለዚህም መጀመርያውኑ ዘሎ ከመጋባት ሽማግሌ መላኩ ለሚጋቡትም ሆነ ለቤተሰብ ክብርም ጭምር እንደሆነ ይገልጻሉ። ተጋቢዎች በትዳር ዘመናቸው ችግር ቢያጋጥማቸው ወይንም በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር የሚጠሩት ሲጋቡ ሽምግልና የተላኩትን ወይንም ሽማግሌ ሆነው እንዲጋቡ ያደረጓቸውን ነው። ‹‹አንተም ተው፤ አንቺም ተይ፤ ብለው በትዳራቸው ፀንተው እንዲኖሩ መክረውና ዘክረው ያስሟሟቸዋል›› በማለት ነበር መልካም ጎኑን ለወይዘሮ ፋጤ ሲነግሯቸው የነበረው።

አሁንም ወንዱ ወደ ሴቷ ቤት ሽማግሌ መላኩ የቀረ ባይሆንም፤ ሥርዓቱ ግን ተለውጧል፤ ኢትዮጵያዊ ባህልም አይደለም ብለው ነበር የተከራከሩት። እርሳቸው ትዳር ከያዙበት ዘመን ጋር አሁን ያለው ሥርዓት የተገላቢጦሽ ነው የሆነባቸው። እርሳቸው እንዳሉት በእርሳቸው ጊዜ በልጆች የትዳር ሁኔታ ላይ ወላጆች ሚና ነበራቸው። አሁን ላይ ደግሞ ወላጆች እንግዶች ናቸው። ተጋቢዎቹ ሁሉንም ነገር ከጨረሱ በኋላ ነው ወላጆች የሚያውቁት።

ሽማግሌ የሚላክበት ቀን ተነግሯቸው ደግሰው እንዲጠብቁ ነው የሚደረገው። በሽምግልና ወቅትም ሽማግሌዎችን መጠየቅ ያለባቸውን ነገሮች እንኳን አይጠይቁም። ቢጠይቁም የሚለወጥ ነገር የለም። ሙሽሪትና ሙሽራውም ሽምግልና በተላከበት ቀን ይገናኛሉ። ይህ ሁኔታ እየተለመደ በመምጣቱም ልክ እንደ ባህል ተወስዷል።

ወይዘሮ ይመናሹ ነገሩ ውድድር ውስጥ ገብቷል ይላሉ። በድግሱና በሚላኩ ሽማግሌዎች አንዱ ከሌላው በልጦ ለመታየት የሚደረገውን ጥረት ማለታቸው ነው። እነእከሌ የላኳቸው ሽማግሌዎች መባልም እንደ አንድ መስፈርት የመወሰዱ ጉዳይና የኃይማኖት አባቶች ሳይቀሩ ለሰርግ ሽምግልና የመላካቸው ሁኔታ ጥያቄ እየፈጠረባቸው ነው።

እንደ ወይዘሮ ይመናሹ እምነት የኔ ከሌላው ይበልጣል ካልሆነ በስተቀር በወዳጅ ዘመድ፣ በጎረቤት ሽማግሌ የሚሆን ሰው ጠፍቶ የኃይማኖት አባቶችን መላክ የሚያደርስ ነገር አይደለም። ተጋቢዎቹ ቀድመው የጨረሱትን ጉዳይ ለምን ማግዘፍ አስፈለገ? የሚለው ነው ያልገባቸው። ድግሱና የሚላኩት ሽማግሌዎች ቅንጦት እንጂ ባህልና ወግን ለማክበር ነው ብለው አያምኑም።

‹‹የሽምግልና ሥርዓቱን እንዲያደምቁ ነው መሰለኝ ቤተሰብ ወዳጅም ይጋበዛል። የተለመነችውም በእለቱም አምራና ደምቃ ነው የምትውለው። ሰርግ ነው ወይንስ ሽምግልና ነገሩ ግራ ያጋባል›› ሲሉ የገለጹት ወይዘሮ ይመናሹ ለጨዋታ ያነሱት ነገር ያበሳጫቸው ይመስላል። እየተደረገ ያለው ነገር ኢትዮጵያዊ ባህል እንዳልሆነ ነው ቆጣ ብለው ሲናገሩ የነበረው።

ወይዘሮ ፋጤም በሃሳባቸው ይስማማሉ። ምንም እንኳን በእርሳቸው እምነት በእስልምናው ሥርዓቱ የተለየ ቢሆንም፣ ዘመኑ መቀያየሩና ከባህል ውጭ የመሆኑን ጉዳይ እርሳቸውም ቢሆኑ ታዝበዋል። የሚፈጠረው አዲስ ነገር ባህልን ማንነትን የሚዘነጋ መሆን የለበትም በሚለውም ወይዘሮ ፋጤ ይስማማሉ።

ወይዘሮ ፋጤና ወይዘሮ ይመናሹ ሌላው በጨዋታቸው ያነሱት የአጥር ወፍ አትይሽ ጉዳይ ነበር። አሁንም ወይዘሮ ይመናሹ ናቸው ሃሳቡን የጀመሩት፤ እርሳቸው እንዳሉት የአጥር ወፍ አትይሽ የቆየ የኢትዮጵያ ባህል ነው። ጥሩ ባህልም ነው። አንዲት ለመውለድ ቀኗ የደረሰ ሴት ያዘጋጀችውን የገንፎ እህል ለማስቀመስ ጎረቤቶችዋን፣ ወዳጅ ዘመዶችዋን ሰብስባ ገንፎ ታቀምሳለች።

የዚህ ሥርኣት ዋናው ዓላማ ምጧ ቀላል እንዲሆንላት፣ በጤና በሰላም እንድትገላገል፣ ጤነኛ የሆነ ልጅ እንድትወልድ፣ ልጇን ለማቀፍ እንዲያበቃት፣ በአጠቃላይ መልካም ምኞታቸውን እንዲገልጹላት ነው። በተለይም በእድሜ የገፉ ሰዎች ምርቃት ጥሩ ነው ተብሎ በባህሉ ስለሚታመን ምርቃታቸውን ለማግኘት በጣም ስለምትፈልግ ለመውለድ ቀኗ የደረሰ ሴት ገንፎ ታዘጋጃለች። ጎረቤትም ቢሆን ገንፎ የሚቀምስበትን ቀን በጉጉት ነው የሚጠብቀው።

ይሄ መልካም የሆነ ኢትዮጵያዊ ባህል እንደሆነ የሚገልጹት ወይዘሮ ይመናሹ፤ አሁን ላይ ‹‹ቤቢ ሻወር›› ተብሎ ስሙም ተቀይሮ በሆቴል ቤት ውስጥ ሁሉ ሳይቀር መዘጋጀቱን አልወደዱትም። አንዳንዶችም ነፍሰጡሯ ሳታውቅ የተለያዩ ነገሮችን አዘጋጅተው በመጥራት ለማስደነቅ የሚሞክሩትንም አግባብ ነው ብለው አያምኑም። ዓላማውን የሳተ ነው ይላሉ።

አንዳንዶቹም ለሰርግ የሚደረግ ዝግጅት ያህል ነው የሚዘጋጁት። ይሄም ቢሆን ሽምግልና ሲላክ ከሚደረግ ዝግጅት ያልተናነሰ መሆኑ ጉረቤታሞቹ እንግዳ ሆኖባቸዋል። ጎረቤታሞቹ እንዲህ ያለው ነገር ቅጥ ያጣና ኢትዮጵያዊ ባህል እንዳልሆነ ነው የተነጋገሩበት። የራስ የሆነን የባህል እሴት ትቶ የሌላውን መከተል ከኢትዮጵያዊነት ያፈነገጠ ነው ሲሉም ነው የገለጹት።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# አዲስ መንገድ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ጥበብን ለምትፈልጓትና ፈልጋችሁም ላጣቿት፤ ጥበብ ወዲህ ናት... ሰሞኑን ከአንድ አዲስ መንገድ ላይ ጉዞ ጀምራለች። ከሰሜን እስከ ምሥራቅ፣ ከደቡብ እስከ ምዕራብ ጓዛቸውን ሸክፈው ሁሉም አዲስ አበባ ላይ ይከትማሉ። ቱባ ቱባ ባህሎች ፍሪዳ ፍሪዳ ጥበባት ጥለው፣ ሙዳውን ከጮማው እየቆረጡ ሊያበሉን ሳይሆን አይቀርም። እኛ ካልቀረን በስተቀር ጥበብማ ቀድማን ደርሳለች። አራቱንም ማዕዘናት በአንድ መድረክ ላይ ያገናኘ የኪነ ጥበብና የሥነ ጥበብ ውድድር አሐዱ የተባለበትን የባህል ሸማ ተለብሶ በትእይንቱ እሽቅርቅር ሊባልበትም ታስቧል። ማነውስ አሳቢው? ከተባለ፤ የኢትዮጵያ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሲሆን ለዚህ ደግሞ እኔ አለሁኝ ይላል።

በታሪኩ የመጀመሪያው የሆነውን ሰፊ የጥበብ ገበታ አዘጋጅቶ ሸርጉድ ማለቱን ተያይዞታል። ከብዙ የሸርጉድ ሌትና መአልት በኋላ ቀኑ ደርሶ ጠሪ አክባሪውን በመቀበል የአዳራሹን በር፣ የመድረኩን መጋረጃ ገልጦ እንደቆመ ነው። ጥበብም መቀነቷን አጥብቃ ሰንዳ ትላለች። እኛም እሷኑ ተከትለን እብስ ማለታችን አይቀሬ ነው። በዛሬው ዕለተ ሐሙስ ሰኔ 13 ቀን፤ ከኢትዮጵያ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ደጃፍ ተነስታ በጊዮን ሆቴል አዳራሽ ውስጥ ሽብርቅ ትላለች። በባህል ቀሚሷ አምራና ደምቃ ገና በጠዋቱ ከማለዳው የብርሃን ጮራ ጋር ስታንጸባርቅ ለማየት እኛም እንቸኩላለን።

"የባህል ጥበባት ለማኅበረሰብ ትስስር እና ለሀገረ መንግሥት ግንባታ" ይላል የዓላማው አትሮኖስ ከተራራው ላይ ሽቅብ እያበራ። ኪነ ጥበቡን ለመዝናናት ብቻ የምንፈልገው ከእንግዲህ ወዲያ አንፈልገው። ከዚህም ያለፈና የገዘፈ ምንነት እንዲኖረው በተረሳበት ደጅ ሁሉ አሁን ታውሷል። አሁን ላይ አንድም ከባህል ጉብታ ላይ ወጥቶ፣ ሁለትም ከሀገር ግንባታ ላይ ተሰማርቶ ታላቅነቱን ለማሳየት የሚችልበትን ዕድል ወደማግኘቱ ላይ ነው። ዕድሉን ካገኘማ ሁለቱንም ባላዎችን አንድ አድርጎ ያማረ ትርኢት ያሳየናል። ከሰሞኑ የተሰማው አዲስ መንገድ ደግሞ ወደ ሀዲዱ መግቢያው ነው። "መቼ ነው ግን መንግሥት ዞር ብሎ ኪነ ጥበቡን የሚመለከተው?" ብለን ስንጠይቅ ለነበርንም ቢያንስ የአፍታ እፎይታን የሚሰጠን ይሆናል። ኪነ ጥበባትና ሥነ ጥበባት ከሁሉም የውብ ባህል ህብረ ብሔሮች ጋር እንደ ሀገር በአንድ መድረክ የታዩበትን ጊዜ ለማስታወስ ያዳግታል። ያሉን ነገሮች የማይነጥፉ የባህል እሴቶች ብቻም ሳይሆኑ፤ የማይነጥፉ ህብረ ጥበባትም ጭምር ናቸው። እናም ባህሎቻችንን ከኪነ ጥበባትና ሥነ ጥበባት ጋር ሲነሰነሱ ልንመለከታቸው ነው። ከእያንዳንዱ የሀገራችን ክፍል የተወከሉ ተወዳዳሪዎች ደርሰዋል። በተለያዩ ዘርፎች ለማወዳደር የተመረጡ ቁንጮ ዳኞችም ዝግጁ ሆነው በመጠባበቅ ላይ ናቸው። ዛሬ ሰኔ 13 ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 15 ቀን ድረስ ለተከታታይ ሦስት ቀናት ይዘልቃል። ከውድድሩ በተጨማሪም ትርኢታዊ ትእይንቶች የሚቀርቡ ይሆናል።

2016፤ ወርሀ ሰኔ፣ የመጀመሪያውን ዙር ለማዘጋጀት የተመረጠች ዕድለ ጥበብ ሆናለች። ቀጣዩን ለሚቀጥለው ዓመት ከሰጠን በኋላ ቀጥሎስ? ስንል... ወዲሁ ይመልሰንና ታዲያ እንዴትና በምንስ ይሆን ውድድርና ትእይንቱ? ማለት አይቀርም። የዝግጅቱ ዋና አጋፋሪ የሆነው የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፤ ከሳምንት በፊት ከሚዲያ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ቢጤ ምክረ ሃሳብ አድርጎ ነበርና ከነገሩን እናጋራችሁ...በዘንድሮው የመጀመሪያ ዙር አራት ያህል ጥበባት የተመረጡ ሲሆን አንደኛው ግን ለኤግዚቢሽን ትርኢት የሚውል ይሆናል። እያንዳንዱ የክልልና የከተማ አስተዳደር ተወዳዳሪዎቻቸውን ይዘው ይቀርቡባቸዋል የተባሉት ዘርፎችም ሙዚቃ፣ ስዕልና ፋሽን ናቸው። በሙዚቃው ዘርፍ በድምጽና በሙዚቃ መሣሪያዎች ሲሆን እያንዳንዱ የሚቀርብበት መንገድ የራሱን የባህል ሙዚቃ በሚያንጸባርቅ መልኩ ይሆናል። በስዕል ዘርፍ ወጣትና ልምድ ያላቸው ሰዓሊያን በሁለት ጎራ ይሳተፋሉ። በፋሽኑ ደግሞ በወንድና በሴት ሞዴሎች ተለይቶ ይደረጋል።



ይህ ሁሉ ሲሆን ውድድሩ በምን ልኬትና ሚዛን ነው አሸናፊውን ለመለየት የሚቻለው? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም፤ ምክንያቱም ውድድሩ በግለሰብ ደረጃ ሳይሆን ባህላቸውን ይዘው በቀረቡ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል ነውና። "እኛ ሥራውን እንጂ ባህልን ከባህል አናወዳድርም" ሲሉ ተናግረው ነበር፤ በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የኪነ ጥበብና ሥነ ጥበብ ዘርፍ ኃላፊዋ ክብርት ነፊዛ አልማህዲ ከሚዲያዎች ጋር በነበራቸው ቆይታ። ዶሮ ወጥ አሊያም ሽሮ ወጥ ሠርቶ ማቅረብ ማንም የማይጋፋው መብት ነው። የዳኛው የምግብ ምርጫ ዶሮ ወጥ ስለሆነ አሸናፊ እንዲሆን አያደርገውም። ሽሮ የሚወደውንም እንዲሁ... ዶሮ ወጥ አቅራቢው የሚወዳደረው ከሽሮው ጋር ሳይሆን ከሚታወቀው የዶሮ ወጥ አሠራርና ጣዕም ጋር ነው። ማንኛውም ተወዳዳሪ ይገልጸኛል የሚለውን ምንም ነገር ይዞ መቅረብ ይችላል። ነጥብ የሚያስገኝለት ይዞ የመጣው ነገር ሳይሆን ይዞ የመጣውን ነገር የሚያቀርብበት መንገድ ነው። ስለዚህ ከተወዳዳሪው ፊት የተቀመጡት ዳኞች ሚዛኖቻቸውን የሚያስቀምጡት ከራሱ ከብሔረሰቡ ትውፊታዊ መስፈርቶች ላይ ይሆናል። የሚቀርቡት ተወዳዳሪዎችም እዚህ የደረሱበት መንገድ ቀደም ሲል በየክልልና ከተሞቻቸው ከታች ከወረዳ ጀምሮ እየተወዳደሩ እንጂ በዘፈቀደ ተመርጠው የመጡ አለመሆናቸውንም ክብርት ነፊሳ አውስተውታል። በእያንዳንዱ ዘርፍ አሸናፊ ለሚሆኑትም የማበረታቻ ሽልማቶች ስለመኖራቸውም ገልጸዋል።

ኪነ ጥበብ ሀገረ መንግሥትን ለመገንባት ምሰሶና ዋርካ መሆኑን አሁን አሁን መንግሥትም እያመነና ለመሥራት እያሰበበት ያለ ይመስላል። ከዚህ ቀደም እንደምናውቀው ለሀገር ግንባታው ቀርቶ ከመዝናኛነትና ከጊዜያዊ የስሜት ቋጥኝ ያለፈ መቀመጫ አነበረውም። በመሪ ቃሉ ላይ ከተቀመጠው አንጻር ብቻ አንድ ርምጃ ወደፊት ልንለው እንችላለንና ይህም አንድ አዲስ መንገድ ነው። ኪነ ጥበብ ከተጠቀሙበት ሀገርን እንደ ባቢሎን የመሥራት አቅም አለው። እንደ ሀገርም እንደ ዓለምም ፖለቲካን በፖለቲካ ከመፍታት ይልቅ፤ ፖለቲካን በኪነ ጥበብ መፍታት ጊዜ፣ ገንዘብና ነብስንም ቆጣቢ ነው።

በባህል እሴት ለታጨቅን እኛ እንዲህ ዓይነቱ ባህል ወለድ ኪነ ጥበባዊ መንገድ ፍቱን መድሃኒታችን ነበር። ነገሩ ግን ለመረዳት እጅግ የዘገየን ይመስላል። ልንጠለልበት የምንችልበትን ትልቁን ዋርካ እንደ ጉቶ ስንቀመጥበት ብቻ ኖረናል። ከሰው ልጆች አፈጣጠር ጀምሮ እድሜ ጠገብ የሆነውን ኪነ ጥበብ እስካሁንም ድረስ "አቡሽና ሚጣ" ብለን በምንጠራው ደረጃ ላይ መሆኑ ያሳዝናል። ሌላው ቀርቶ ከያሬድ ጀምሮ ያለው ሙዚቃ፣ ዋሻና አለቱን እየፈለፈሉ ስዕልና ቅርጻ ቅርጽን የጀመሩበት፣ ቆዳውን ድጠውና አልፍተው በብራና ላይ የከተቡበት ዘመን ብናስብ እንኳ አንቱ የሚያንሰው ነበር። አዲስ ነገር ልንሠራባቸው ባንችል እንኳን ተገቢውን ክብርና ዕውቅና ሰጥተን ልንከባከባቸው ይገባን ነበር። በየጓዳው ተሰግስገው ሳንጠቀምባቸውና ሳንጠቅማቸው ከገሚሱ ተፋጠን ከገሚሱም ተጠፋፍተን ኖረናል። አሁን ግን እንደ አንድ ሀገር መንግሥት ጠቀለል አድርጎ ለመሥራት መታሰቡ ይበል የሚያሰኝ ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በነበረው አሠራር የኪነ ጥበብ ዘርፍ ይመራ የነበረው እንደ አንድ ክፍል ነበር። ከሦስት ዓመታት ወዲህ ግን እራሱን ችሎ በሚኒስትር ደረጃ እየተመራ የተሻለ ትኩረት ለማግኘት ችሏል። በሀገር ደረጃ የጥበብ ባለ እዳ ነን። ጥበብ ካሳ ይገባታል ቢባል፤ በምንም መልኩ እዳዋን ከፍለን የምንጨርሰው አይደለም። የአሁኑ አዲስ መንገድም የእስከዛሬውን ስብራት ለመጠገን በማሰብ ይመስላል።

ግን ደግሞ አንድ ነገር ያሰጋናል...በኛ ሀገር ውስጥ የሚጀመሩ ብዙ ነገሮች፤ ጊዜ ሁኔታውን ግራና ቀኙን እየተመለከቱ መሀል ላይ ደብዛቸው የሚጠፋው ነገር አለ። ከመንግሥት ለውጥ ጋር ተያይዘው የሚለዋወጡ ጉዳዮች ቀላል አይደሉም። አሁን የተጀመረው በመንግሥት እንደመሆኑ፤ ታዲያ ለወደፊቱስ ምን ታስቧል? የሚል ጥያቄ እንድንጠይቅ ያስገድደናል። የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እንደጀመረው በነካ እጁ የወደፊቱንም ህልውናውን ቢቀይሰው መልካም ነው። የጥበባት ኢንዱስትሪዎች እና የግሉን ባለሀብቶች በማካተት፤ ቀስ በቀስ እራሱን የቻለ አንድ ግዙፍ ተቋም አድርጎ የማይሻር የማይለወጥ ማድረግ ይኖርበታል። አሊያማ የሚሰበር እስካለ ድረስ ሰባሪው ብዙ ነው። በሚገባው ልክ ተይዞ ከተኬደበት መንገዱ ወደ ታላቅነት ነው። እራሱን እያንበሸበሸ በሀገር ኢኮኖሚው ላይ ብትን አበባ ይነሰንስበታል።

ውድድሩን ፊት ለፊት በደመነብስ ብቻ ከተመለከትነው ባህልን ከባህል ጋር የማወዳደር ብዥታ ይደነቀርብን ይሆናል፤ ያ ግን እውነት አይደለም። ከውድድሩ በፊትም ሆነ በኋላ ሁሉም አንደኛ ናቸው። ተወዳዳሪዎቹ ወደ መድረኩ ሲወጡና ይዘው የመጡትን በዳኞች ፊት ሲያቀርቡ በኪነ ጥበባዊና በውበት ሚዛን ይለካሉ። ስለዚህ አዲስ ፈጠራ አዲስ እይታን መፍጠር ይኖርባቸዋል። ፈጠራው ግን ያነበረውን መፍጠር ላይ ሳይሆን የነበረውንና ያለውን ማራኪ በሆነ መንገድ የማቅረብ ነው። ሁሉም ተወዳዳሪ ዶሮ ወጥ ይዞ እንደሚያቀርብ ዳኞች ቀድሞም ያውቁታል፤ ስለዚህ ነጥብ የሚያሰጠው ያቀረቡት ዶሮ ወጥ ሳይሆን ጥፍጥናው ላይ ነው። ያ ደግሞ በተወዳዳሪው የግል ችሎታ ላይ እንጂ በባህሉ ላይ የተመረኮዘ አይደለም። ከዳኞች ፊት በጋሞ ብሔረሰብ ጭፈራ የቆመ አንድ ሰው የሚለካው ከሚጨፍርበት ሙዚቃ ጋር በተዋሃደበት መጠንና ጋሞኛ ጭፈራ ከሚጠይቀው እንቅስቃሴያዊ ችሎታ አንጻር ብቻ ነው። ከዳኞቹ ይልቅ ብሔረሰቡ ባስቀመጠውና በሚያውቀው መስፈርት ላይ የተደገፈ ይሆናል።

ውድድሩ እንደ ውድድር ብቻ ተካሂዶ እጅ የሚጣፋበት አይደለም። ከዚህ በስተጀርባ ሌሎች ግዙፍ ዓላማዎች እንዳሉት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሚዲያ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በነበረው የውይይት ወቅት ገልጾ ነበር። ከሃሳቡ ውስጥ ሦስት አንኳር ነጥቦችንም ለመጥቀስ እንችላለን። የመጀመሪያው ነገር የጅምሩን ቀጭን መንገድ ይዞ እስከ ክልልና ዞን፤ አልፎም እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ መዘርጋት ነው። ከላይ ቢጀምርም የሚያስፈልገው ግን ከታች መጀመርን ነው። ሰፊ ጊዜና ዝግጅት ቢሻም እንደ ወርቅ እየተፈተነ በስተመጨረሻ በሀገር ደረጃ የምናገኘው የነጠረውን ንጽሁ ወርቅ ይሆናል። ሁሉንም የኢትዮጵያን ባህልና ጥበብ የምናውቀው ይመስለናል እንጂ ገና ምኑም አልተነካም። ካለው አንጻር ምንም የምናውቀው የለም። በእንዲህ ዓይነቱ ከባህል ተራራ ስር ከሚቀዳ የጥበብ ምንጭ፤ ከእያንዳንዱ ገጠርና ከተማ እስከዛሬ ድረስ ካልታዩና ካልተሰሙ አዳዲስ ነገሮች ጋር ፊት ለፊት እንገናኛለን። የዚያን ጊዜ ታዲያ፤ ጥበብስ ቢሆን በሀገር ምድሩ ተምነሸነሸችበት ማለት አይደል... ሌላኛውና ሁለተኛው ጉዳይ እስከዛሬ ሲደረግ የምንመለከተውን በተናጠልና የሚደረገውን እንደ አይድልና የተሰጥኦ ውድድሮች የመሳሰሉት ናቸው። በአንድ አሊያም በጥቂት ግለሰቦች ጫንቃ ላይ ያረፉ በመሆናቸው ተጀምረው ሁለትና ሦስት ዓመታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሲቋረጡና እንደ ጠዋት ጤዛ ሲረግፉ ተመልክተናል። በተደራጀ መንገድ የሚደግፉቸውም ሆነ የሚያንቀሳቅሳቸው ተቋም ባለመኖሩም ዝብርቅርቅ ወለፈንዲ ናቸው።

ችግሩን ለመቅረፍ እንዲህ በተቋም ደረጃ መያዙ አንደኛው የመፍትሄ መርፌው ነው። ይህቺን ዘለል ለማለት ስንችል ደግሞ ሦስተኛው ይመጣል። መንግሥት የዘርፉን ጠቀሜታ ተረድቶ ይበልጥ እንዲጠጋና እንዲደግፈው ያደርጋል። መንግሥትን ከኪነ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብን ከሕዝብ ጋር በሦስት ማዕዘናት አቆራኝቶ ሁሉንም በእኩል ያስጠቅማል። ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ኪነ ጥበባዊ ጉዳዮቻችን ሰከን ደልደል እንዲሉ ያስችላቸዋል። በሚመጣው ትውልድም እንደ ሀገር ምን ሠሩ ብንባል፤ ይኸው...ተብሎ የሚጠቀስልን ይሆናል። በዚህ መንገድ አጠንክረን ለመሄድ ከቻልን ለውጥ የማንፈጥርበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ወደኋላኛው ዘመን መለስ ብንል እንኳን በሕዝብ ለሕዝብ ሀገራችን የማያልቅ ኪነ ጥበባዊ በረከትን አግኝታበታለች። ከዚሁ አልፎ ወደ ውጭ ሀገራት ሁሉ በርካታ ኪነ ጥበባዊ ጉዞዎች ይካሄዱም ነበር። ፖለቲካው ሊከፍታቸው ያልቻላቸውን በሮችንም ጭምር ኪነ ጥበቡ ይከፍተዋል። ምን ያህል ጠቅሞናል አሊያም ይጠቅመናል የሚለውን የሚያውቀው ያውቀዋል።

ኪነ ጥበብ ያለ ሚዲያው በጎ ፈቃድ የማይታሰብ ነው። ምክንያቱም አብዛኛው የኪነ ጥበብ ማዕድ የሚቀርበው ከሚዲያና በሚዲያ በመሆኑ ነው። ይህንንም በመረዳት ይመስላል አዘጋጅ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስቀድሞ ከሚዲያዎች ጋር የግንዛቤ ፈጠራና የውይይት ምክረ ሃሳብ መድረክ ማዘጋጀቱ። እያንዳንዱ ሚዲያስ? ኪነ ጥበቡን በእጁ እንደያዘ ተረድቶ በምን ያህል ደረጃ እየሠራበት ይሆን? የሚለውም ምላሹ የሚዲያው የራሱ ነው። በርከት ያሉ ኪነ ጥበባዊ የመዝናኛ ሚዲያዎች ቢኖሩም ባህልና እሴቶቻችን ከነባለቤቶቻቸው የሚንጸባረቁበት ሜዳ ጠባብ መሆኑ ነው። ለመቦረቅም ለማስፈንደቅም አይሆንም።

ይህ ሁሉ መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ አይደለም። ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል፤ በትንሽዬዋ ጅምር ውስጥ ከዛሬ ይልቅ የነገው ኪነ ጥበብ ቆሞ በእግር ሲሄድ ለመመልከት ያጓጓናል። ለዚህ ዓመት የተመረጡት የኪነ ጥበብና ሥነ ጥበብ ዘርፎች ካሉት አንጻር በጣም ጥቂቶቹ ናቸው። በቀጣይ እየጎመራ ሲሄድ ፊልምና ቲያትሮችንም ለመመልከት እንደምንችል ተስፋ እናደርጋለን። እርግጥ ነው ገና ከጅምሩ በአንድ ጀንበር ሁሉን ለማካተት አይቻልም፤ ቢሆንም ግን ሥነ ጽሁፉ ሊዘለል አይገባውም ነበር። ከሁሉም አንጻር ለዳኝነቱም ሆነ ለዝግጅቱ እምብዛም የሚከብድ አይደለም። ሥነ ጽሁፍ ያልተካተተበት የኪነ ጥበብ ጉባኤ ፀበል ጻዲቅ የጎደለው ማህበር ይሆናል። አብዛኛዎቹ የጥበብ ዘርፎችም ከሥነ ጽሁፉ ጋር የተሳሰሩም ጭምር ናቸው። ኮሜዲውም ድሮ ድሮ በየትኛውም የጥበብ ድግስ ድንኳን ሰባሪ ነበር። አሁን አሁን በብዙ ቦታዎች ላይ የመረሳት አደጋ ይጋረጥበታል። ለቀጣዩ ዕድል አግኝተው ሊታሰብባቸው ከሚገቡ ነገሮች አንደኛው የኮሜዲው ዘርፍ ነው።

እንግዲህ አዲሱ መንገድ ብዙ ካፈጠጡበት እሩቅ ያስኬዳል። ከውድድሩ አስቀድመን በረዥም መንገድ ውስጥ እንዳንጠፋና እንዳንጠፋፋም፤ አቅጣጫ ጠቋሚ ግብዣችንን ወደ ጊዮን ሆቴል በመቀሰት፣ ጋባዦቹ ግን ከወዲሁ መመለሳችን ነው። ጥበብን ለምትፈልጓት ከዚያው ትጠብቃችኋላች።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ግንዛቤና ትኩረት ለሚጥል ሕመም

አስናቀ ፀጋዬ

ወይዘሮ እናት እውነቱ የሚጥል በሽታ ታማሚ ናቸው። አብዛኛውን ሕይወታቸውን ያሳለፉት በእንግሊዝ ሀገር ነው። በኖሩበት እንግሊዝ ስለሚጥል ህመምና መደረግ ስላለበት የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ትምህርት የሚሰጠው ገና ከታዳጊዎች ጀምሮ ነው። መንገድ ላይ ሰው ቢወድቅ የስድስትና የሰባት ዓመት ልጅ ምን ማድረግ እንዳለበት ያውቃል። በዛ ሀገር የሚጥል ህመም ምንም ማለት አይደለም። ብዙ ነገሮች ለታማሚዎች የተመቻቹ በመሆናቸው ህመሙ ቀሎ ነው የሚታየው። በውጪው ዓለም የሚጥል ህመም ያለበት ሰው ሲወድቅ ልክ እግር ኳስ ተጫዋች እንደወደቀ ያህል ነው የሚቆጠረው። ታዲያ የወይዘሮ እናት ምኞትም ልክ በእንግሊዝ ሀገር እንደተመለከቱት ከሚጥል ህመም ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ እዚህ ደረጃ ላይ እንድትደርስ ነበር።

የኅብረተሰብ ጤና ስፔሻሊስቷ ወይዘሮ እናት እውነቱ ዛሬ ላይ ‹‹ኬር ኢፕሊፕሲ ኢትዮጵያ›› የተሰኘና በሚጥል ህመም ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን የሚሰራ ድርጅት መስርተው በዋና ዳይሬክተርነት እየመሩ ይገኛሉ። እርሳቸው እንደሚሉት የኬር ኢፕሊፕሲ ኢትዮጵያ ሥራ በርካታ ዘርፎች ያሉት ሲሆን፤ ዋነኛው ሥራው ግን ከሚጥል ህመም ጋር በተገናኘ ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው። በይበልጥ ደግሞ ድርጅቱ ትኩረት አድርጎ የሚሠራው በትምህርት ቤት ሕፃናት ላይ ነው።

ድርጅቱ ከሚጥል ህመም ጋር ስኬታማ ህይወት መኖር እንደሚቻል ያምናል። በተለይ ሕፃናቶች ትምህርታቸውን ያለሃሳብ መከታተል እንደሚችሉና ተገቢውን እውቀት አግኝተው ነገ ራሳቸውንና ሀገራቸውን መጥቀም እንደሚችሉ አምኖ ይሠራል። ሕፃናት እስኪያድጉ ድረስ በተወሰነ መልኩ ቤተሰብ ይንከባከባል። እድሜያቸው ከፍ እያለ ሲመጣና ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ሲያጡ ብዙዎቹ



ወይዘሮ እናት እውነቱ፤

የጎዳና ተዳዳሪ ይሆናሉ። በተለይ ከክልል የሚመጡ በርካታ የሚጥል በሽታ ታማሚ የጎዳና ሕፃናት በአዲስ አበባ ጤና መዋቅር ውስጥ ስላልታቀፉ ሕክምናና መድኃኒት አያገኙም። ከዚህ ችግር በመነሳት ድርጅቱ ከጤና ተቋማትና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመሆን ሕፃናቱ መድኃኒታቸውን ማግኘት እንዲችሉ እያደረገ ነው።

ዋና ዳይሬክተሯ እንደሚገልጹት፤ የሚጥል ህመም ያለባቸው ሕፃናት በርካታ ተፅእኖ ይደርስባቸዋል። የሚጥል ህመም ያለባቸው ሕፃናት የሀኪሞች ቁጥርም ዝቅተኛ ነው። አሁን ያለው የሀኪሞች ቁጥርም 7 ሲሆን፤ እነዚህ ሀኪሞች ሥራቸውን የሚያከናውኑት በአብዛኛው እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ከ5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የሚጥል ህመም ታማሚዎች እንዳሉ ይገመታል። ከዚህ አንፃር በተለይ በክልል የሚገኙ የሚጥል ህመም ያለባቸው ሕፃናት በአብዛኛው የሕክምና አገልግሎት አያገኙም።

ህክምናው በክልል እንደልብ አለመኖሩ ደግሞ ከፍተኛ ጫና ያመጣል። ሕፃናቱም ያለባቸውን ህመም መግለፅ አይችሉም። ከእነርሱ ይልቅ ስለህመማቸው የሚናገሩላቸው ወላጆቻቸው ናቸው። በርግጥ ሁሉም የሚጥል ህመም ይጥላል ማለት አይደለም። የማይጥል ግን በርካታ የሚጥሉ የህመም አይነቶች አሉ። የሚያፈዙ ብዙ አይነት የሚጥል ህመሞች አሉ። ስለዚህ ሕፃናትን በደንብ ህመማቸውን የሚያስተውል የለም። ከዚህ አንፃር ድርጅቱ በተማሪዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በመምህራን ላይም ከበሽታው ጋር በተያያዘ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ያከናውናል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሚጥል ህመም ታማሚ ሕፃናት በትምህርት ቤትም አሉታዊ ተፅዕኖ ይደርስባቸዋል። ለምሳሌ አንድ ሕፃን በህመሙ ምክንያት እንደወደቀ መጀመሪያ ከትምህርት ቤት ነው የሚወጣው። ስለዚህ ድርጅቱ በሚጥል ህመም ምክንያት ከትምህርት ቤት የሚቀሩ በርካታ ተማሪዎችን እየታገለ ዳግም ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ጥረት ያደርጋል። የሚጥል ህመም ሲያጋጥም ምን ማድረግ እንደሚገባ መምህራንና ተማሪዎችን በማሰልጠን ተማሪዎች ወደትምህርት ገበታቸው እንደሚመለሱ ብዙ ሥራዎችን ሠርቷል።

የሚጥል ህመምን በሕፃናት ላይ ከሚያባብሱ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ስጋት እንደመሆኑ በተለይ ተማሪዎች በፈተና ወቅት በሚገባቸው ስጋት ምክንያት በተደጋጋሚ ስለሚወድቁና ይህ ድርጊት ደግሞ በመምህራን ዘንድ ውሸት እንደሆነ ስለሚታሰብ ተማሪዎቹን ከፈተና ያባርሯቸዋል። ይህ ደግሞ አመቱን ሙሉ የተማሩት ትምህርት ባከነ ማለት ነው። ህመሙ ሕፃናት ላይ ከህክምናውም፣ ከህብረተሰቡም፣ ከትምህርትም አንፃር አሉታዊ ተፅእኖ አለው።

ስለዚህ ከሚጥል ህመም ጋር በተያያዘ በሕፃናት ላይ ለውጥ ማምጣት ካልተቻለ የቀጣይ ሕይታቸው ጨለማ ነው የሚሆነው። ለዛም ነው ድርጅቱ በይበልጥ ሕፃናት ላይ ትኩረቱን አድርጎ እየሠራ ያለው። ድርጅቱ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በጋር እየሠራ ያለ ቢሆንም የሚፈልገውን ያህል ትብብር እያገኘ አይደለም።

ዋና ዳይሬክተሯ እንደሚያብራሩት ድርጅቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሥራውን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ ግን በአቅም ውስንነት ምክንያት በይበልጥ በአዲስ አበባ ከተማ ባሉ የሚጥል ህመም ታማሚ ሕፃናት ላይ ትኩረቱን አድርጎ ይሰራል። ይሁንና አንዳንዴ በክልሎች ለመምህራን በሚጥል ህመምና የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ አሰጣጥ ዙሪያ ስልጠናዎችንና የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ይሰጣል።

በትምህርት ቤት ደረጃ ግን ድርጅቶች በአብዛኛው ሥራውን የሚያከናውነው በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው። ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በ100 ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚጥል ህመም ዙሪያ ለተማሪዎችና መምህራን የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ሰጥቷል። መምህራንን ለብቻቸው አሰልጥኗል። ተማሪዎችም ጓደኞቻቸው ቢታመሙ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመጀመሪያ ደረጃ የህክምና እርዳታ አሰጣጥ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቷቸዋል። በህመማቸው ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡና በድርጅቱ ጥረት ዳግም ወደ ትምህርት ገበታቸው የተመለሱ ሕፃናትም የትምህርት ቁሳቁሶች ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል።

በተመሳሳይ ወላጆችም ከሚጥል ህመም ጋር በተያያዘ ግንዛቤው ኖሯቸው ልጆቻቸውን እንዲንከባከቡ በየወሩ ለወላጆች ብቻ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ የእርስበርስ አቻ ግንኙነት፣ ስብሰባና ውይይት እንዲኖርና ስለልጆቻቸው ባህሪ እንዲነጋገሩ፣ እንዲማማሩና ልምድ እንዲለዋወጡ ይደረጋል። በተጨማሪም በየሳምንቱ ወላጆች የምክር አገልግሎት ያገኛሉ።

# ዓለም አቀፍ



## በሃውቲዎች ጥቃት የደረሰባት መርከብ በቀይ ባህር መስመጧ ተነገረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በየመኑ ሃውቲ ታጣቂ ቡድን ባለፈው ሳምንት ጥቃት የተፈጸመባት መርከብ መስጠሟ ተነገረ።

የላይቤሪያን ሰንደቅ አላማ የምታውለበልበውና የግሪኩ “ቱተር” ኩባንያ ንብረት የሆነችው መርከብ በቀይ ባህር መስመጧን የብሪታንያ የማሪታይም ንግድ አስተዳደር አስታውቋል።

“ቁርጥራጮች እና የሚፈስ ነዳጅ መርከቧ ለመጨረሻ ጊዜ በታየችበት አካባቢ ታይቷል” ያለው ተቋሙ፤ ይህም መርከቧ መስጠሟን እንደሚያመላክት ገልጿል።

ሃውቲዎች ከሰባት ቀናት በፊት በውሃ ውስጥ በሚጓዝ ድሮን ጥቃት የተፈጸመባት “ቱተር” መርከብ ስለመስመጧ እስካሁን ማረጋገጫ አልሰጡም ብሏል አሶሼትድ ፕረስ በዘገባው።

ጥቃቱ ሲፈጸም በመርከቧ የሞተር ክፍል ውስጥ የነበረ ፊሊፒናዊ መርከበኛ ህይወቱ ማለፉን የአሜሪካ ባለስልጣናት ቢገልጹም ማኒላ እስካሁን ያለችው ነገር የለም።

በቀይ ባህር በሃውቲዎች ጥቃት መርከብ ሲሰጥም የ”ቱተር” ሁለተኛው ነው።

ባለፈው መጋቢት ወር ማዳበሪያ የጫነችው የብሪታንያ “ሩብይማር” መርከብ በቀይ ባህር መስመጧ ይታወሳል።

እስራኤል በጋዛ የምትፈጽመውን ድብደባ የሚቃወሙት የሃውቲ ታጣቂዎች ከእስራኤል፣ አሜሪካና ብሪታንያ ጋር ግንኙነት አላቸው ባሏቸው መርከቦች ላይ ከ50 በላይ ጥቃቶችን ፈጽመዋል።

ዋሽንግተን ከጥር ወር ጀምሮ አጋሮቿን አስተባብራ በቡድኑ ይዞታዎች ላይ የአየር ጥቃት ስትፈጽመ መቆየቷ ይታወሳል።

ከሦስት ቀናት በፊት በሆዴይዳህ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እና በካማራን ደሴት አቅራቢያ ከብሪታንያ ጋር የአየር ድብደባ መፈጸሟን ነው ሬውተርስ የዘገበው።

ይሁን እንጂ የዋሽንግተን እና ለንደን ድብደባ የሃውቲ ታጣቂዎችን አንድ መርከብ ከመያዝና ሁለት ከማስመጥ አልገታቸውም።

የቡድኑ የድሮን እና ሚሳኤል ጥቃት የመርከብ ኩባንያዎች አቋራጩን የስዊዝ ካናል አይተው በረጅሙ የኬፕ ኦፍ ጉድ ሆፕ (ደቡብ አፍሪካ) መስመር እንዲጓዙ አድርጓቸዋል።

የአሜሪካ የመከላከያ ደህንነት ተቋም በቅርቡ ያወጣው ሪፖርትም በቀይ ባህር የሚያልፉ እቃ የጫኑ መርከቦች ቁጥር ከታህሳስ ወር ወዲህ በ90 በመቶ መቀነሱን ነው የጠቆመው።



## ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ሰሜን ኮሪያ ገቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ሰሜን ኮሪያ ገብተዋል።

ፕሬዚዳንት ፑቲን በትናንትናው ዕለት ፒዮንግያንግ ሲገቡ ደማቅ የተባለ አቀባበል ተደርጎላቸዋል።

አሜሪካን ጨምሮ ምዕራባውያን ሀገራት፣ ፑቲን ሩሲያ በዩክሬን ለምታካሂደው ዘመቻ ሙሉ ድጋፍ ወደሰጠችው ሰሜን ኮሪያ የሚያደርጉትን ጉብኝት በአንክሮ እየተከታተሉት ነው።

ከ24 ዓመት በኋላ ወደ ፒዮንግያንግ ያቀኑትን ፕሬዚዳንት ለመቀበል በኪም ሁለተኛ አደባባይ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወጥቶ እንደነበር ሮይተርስ ዘግቧል።

ይህን ተከትሎ ፑቲን እና ኪም ንግግር ለማድረግ ወደ ኩምሱሳን ቤተመንግሥት አቅንተዋል።

"ሩሲያ በዩክሬን የምታካሂደውን ዘመቻ ጨምሮ ለሩሲያ ፖሊሲ ያለውን ወጥ ድጋፍ በእጅጉ እናደንቃለን" ሲሉ ፑቲን በውይይቱ መጀመሪያ ላይ መናገራቸውን ሮይተርስ የሩሲያውን ሪያ ዜና አገልግሎት ጠቅሶ ዘግቧል።

ፑቲን ሩሲያ የኢምፔሪያሊስቷ አሜሪካ እና አጋሮቿን የበላይነት እየተዋጋች ነው ብለዋል።

ኪም በበኩላቸው የሰሜን ኮሪያ-ሩሲያ ግንኙነት ወደ አዲስ ምዕራፍ እየተሸጋገረ መሆኑን ገልጸዋል።

"አሁን ላይ የዓለም ሁኔታ የበለጠ እየተወሳሰበ እና በፍጥነት እየተቀየረ ነው። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ከሩሲያ ጋር ያለንን ግንኙን የበለጠ እናጠናክራለን" ብለዋል።

ኪም አክለውም ሰሜን ኮሪያ "ሩሲያ ሉአላዊነቷን እና ደህንነቷን ለመጠበቅ በዩክሬን የምታደርገውን ልዩ ወታደራዊ ዘመቻ ሙሉ ለሙሉ እንደግፋለን" ሲሉም ተናግረዋል።

ምዕራባውያን ሰሜን ኮሪያ ሩሲያ በዩክሬን ለምታደርገው ጦርነት ጥቅም ላይ የሚውል የጦር መሳሪያ ታቀርባለች ሲሉ ይከሷታል። ሰሜን ኮሪያ ግን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ነው በማለት በተደጋጋሚ አጣጥላዋለች።

# ስፖርት



# ለሁለተኛው የኦሊምፒክ ወርቅ በዝግጅት ላይ የሚገኘው ሰለሞን ባረጋ

ብርሃን ፈይሳ

በፓሪስ ኦሊምፒክ እንደሚደምቁ ከሚጠበቁ ኢትዮጵያውያን ወጣት አትሌቶች መካከል አንዱ የ10ሺ ሜትር ኦሊምፒክ ቻምፒዮኑ ሰለሞን ባረጋ ነው። በዚህ ርቀት እጅግ ተፎካካሪ የሆኑትን የምስራቅ አፍሪካም ሆነ ሌሎች አትሌቶችን በመፈተን ሁሌም ለውጤታማነት የሚተጋው አትሌቱ በቅርቡ በሚካሄደው ኦሊምፒክ ዳግም የክብር ባለቤት ለመሆን በዝግጅት ላይ ይገኛል።

የ24 ዓመቱ ወጣት አትሌት ምንም እንኳ በአካል ጠንካራ ዝግጅት በማድረግ ላይ ቢሆንም፤ ለአሸናፊነት ይህ በቂ እንዳልሆነ እምነቱ ነው። ይልቁኑ ሩጫ የጭንቅላት ጨዋታም እንደመሆኑ በዚህ ረገድም ራሱን እያበቃ መሆኑን ነው ከዓለም አትሌቲክስ ጋር በነበረው ቆይታ የጠቆመው። ሀገሩን በኦሊምፒክ ለመወከል የሚያስችለውን ዝግጅት በአራራት ጫካ ሲያከናውን የቆየው አትሌቱ በስፔን በተካሄደው የኦሊምፒክ ማጣሪያ ሩጫ ፓሪስ ላይ በ10ሺ ሜትር ውድድር ከሚሰለፉ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል አንዱ መሆኑን አረጋግጧል። ባለፈው ሳምንት መጨረሻ በተካሄደው በዚህ የሰዓት ማሟያ ውድድር ላይ ሰለሞን 26:34.93 በሆነ ሰዓት በመሮጥ፤ ዮሚፍ ቀጄልቻ እና በሪሁ አረጋዊን በመከተል 3ኛ ደረጃን ይዞ



አትሌት ሰለሞን ባረጋ፤

ማጠናቀቁም ነው የብሄራዊ ቡድኑ አካል ያደረገው።

በዚህ ዓመት መጀመሪያ ግላስኮ ላይ በተካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና በ3 ሺ ሜትር የወርቅ ባለቤት የነበረው አትሌቱ፤ አብዛኛውን ትኩረቱን ከውድድር ይልቅ በልምምድ ላይ አድርጎ ነበር የቆየው። ከፍተኛ ዝግጅት ተደርጎበታል በተባለው የቶኪዮ ኦሊምፒክ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን 4 ሜዳሊያዎችን (1 የወርቅ፣1 የብር እና 2 የነሃስ) ሲያስመዘግብ የሀገሩን ባንዲራ በብቸኛነት በድል ያውለበለበው አትሌት ሰለሞን ባረጋ መሆኑ አይዘነጋም። ባለፈው ዓመት በቡዳፔስት በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ቢያገኝም በታላቁ የውድድር መድረክ ግን እንደ ቶኪዮው ሁሉ ሌላኛውን ስኬት ማስመዝገብ የዚህ ዓመት ዕቅዱ መሆኑን የአሶሼትድ ፍራንስ ፕሬስ ዘገባ ያሳያል።

በዚህ ርቀት ነግሳ የቆየችው ኢትዮጵያ ከውጤታማነት ርቃ ሳለች በ2020 የቶኪዮ ኦሊምፒክ ያልተጠበቀው ድል መመዝገቡ የስፖርት ቤተሰቡን ጮቤ ያስረገጠ እንደነበር ይታወሳል። ከሁሉ በላይ አስደናቂ የነበረው ግን በ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀቶች የዓለምን ክብረወሰን ጠቅልሎ ከእጁ ያስገባው ኡጋንዳዊው ጆሹዋ ቺፕቴጊን መርታቱ ነበር። አትሌቱ በ5ሺ ሜትር አሸናፊ የነበረ ሲሆን፤ ሁለተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ለማጥለቅ ቢያቅድም በኢትዮጵያዊው ወጣት ሊመክንበት ችሏል። ይህም የአትሌቲክስ ቤተሰቡን ከሚስቡ ጉዳዮች መካከል የሚመደብ ሲያደርገው ፓሪስ ላይ የኡጋንዳዊያኑን ጨምሮ እሱን ከመሰሉ ወጣት የሀገሩ ልጆች ጋር ለአሸናፊነት የሚደረገው ትንቅንቅ እጅግ አጓጊ ነው።

በወጣትነት እድሜው በርካታ ስኬቶችን በማስመዝገብ ላይ የሚገኘው ሰለሞን አሁን ላይ ተስፋ ከሚጣልባቸው ጠንካራና ተፎካካሪ አትሌቶች መካከል አንዱ በመሆኑ ለሌሎች ወጣት አትሌቶች አርዓያ ነው። በ1992 ዓ.ም በጉራጌ ዞን የተወለደው አትሌቱ በልጅነቱ ሩጫ ላይ ሳይሆን ትምህርት ላይ ብቻ እንዲያተኩር በቤተሰብ ግፊት ቢደረግበትም በግል ጥረቱ አሁን ካለበት ደረጃ መድረሱን ይናገራል። እሱንና ሌሎች ስኬታማ አትሌቶችን መመልከታቸው አሁን ላይ አመለካከት ላይ ለውጥ በማምጣቱ ተተኪ አትሌቶች በተሻለ ሁኔታ ወደ ስፖርቱ በመግባት ላይ ይገኛሉ።

ይሁንና የአትሌቲክስ ፍላጎት ብቻውን ውጤታማ ሊያደርግ እንደማይችልም ነው የሚያወሳው ‹‹በርካቶች የኦሊምፒክ ሜዳሊያ አጥልቀዋል፤ ከእነዚህ መካከል አንዱ እኔ ነኝ። ነገር ግን አሸናፊ የሚኮነው ጥሩ የአየር ሁኔታ፣ በሥነልቦና የተገነባ መሆን አሊያም በተመቻቸ ሁኔታ ስላለ ብቻ አይደለም። ነገር ግን ወርቅ ማግኘት የሚቻለው የአእምሮ ዝግጅት ሲኖር ነው። ለምሳሌ ለኦሊምፒክ የማደርገው ዝግጅት ጠንክሮ ከመስራት ባለፈ አእምሮዬ የሚያስበውን ወደ እውነታ ለመቀየር የሚያስችል መሆን ይኖርበታል›› ሲልም ያስረዳል። ይህንን ተከትሎም በአካልና በሥነልቦና ዝግጅት ማድረጉን የሚጠቅሰው ሰለሞን ለዚህ ኦሊምፒክ ሲል የሌሎች ውድድሮች ተሳትፎን አስወግዶ እንደቆየም ነው የሚገልጸው።

ዝግጅቱ የቶኪዮ ኦሊምፒክ ስኬትን በመመዘን ላይ የተመሠረተም ሲሆን፤ የወርቅ ሜዳሊያው የተገኘበትን የዝግጅት ሁኔታ መለስ ብሎ ከአሠልጣኞቹ ጋር በመተንተን ላይ ይገኛል። ይኸውም በፓሪሱ ኦሊምፒክ እንደ ቶኪዮ ሁሉ ውጤታማ ለመሆን የሚቻልበትን አካሄድ የሚያመለክትም ይሆናል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

### ደ/ማ/ዩ ብ/ግ/ጨ/14/2016

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከመንግስት በተፈቀደለት በጀት የአውትሶርስ እና የዶርሚተሪ አጠባ የአገልግሎት ግዥ በብሄራዊ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለሁለት ዓመት አገልግሎቱን ማግኘት ይፈልጋል ::

**ስለሆነም በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ከዚህ በታች የተቀሱትን መስፈርቶች ማለትም፡-**

1. በዘመኑ እና በዘርፉ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ እና የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት እና የታክስ ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ፣ የተመዝጋቢነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
2. አሸናፊው ድርጅት ለሁለት ዓመት ውል በመያዝ
   i. ሎት 1 የዋናው ግቢ የፅዳት አውትሶርስ
   ii. ሎት 2 የዋናው ግቢ የዶርሚተሪ አጠባ
   iii. ሎት 3 ለጤና ካምፓስ የፅዳት አውትሶርስ
3. ለጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ሎት1 ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር)
   ሎት 2. 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ ብር)
   ሎት 3. የጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ብር 50,000.00 /ሀምሳ ሺህ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም አሰርቶ ማቅረብ የሚችል ወይም በጥቃቅን የተደራጁ ከአደራጃቸው የመንግስት መ/ቤት ከላይ የተገለጸውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ የዋስትና ደብዳቤ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም በማሰራት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች ሁሉ የጨረታ ዶክመንቱን ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ወይንም አዲስ አበባ 4 ኪሎ ከቅድስት ማርያም ቤ/ክርስቲያን ወረድ ብሎ ሮሚና ካፌ ላይ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 7 ከሚገኘው ቢሯችን ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ 15 ተከታታይ ቀናት የማይመለስ ብር 300.00 /ሶስት መቶ ብር/ ለእያንዳንዱ ሎት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዩኒቨርሲቲው ስም በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር 1000017980517 በመክፈል ደረሰኝ በማቅረብ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
5. የጨረታውን ፋይናንሻል ኦሪጅናል እና ቴክኒካል ሰነዶችን ኮፒ ዶክመንት በተለያየ ፖስታ በማሸግ ማቅረብ አለበት፡፡
6, አሸናፊው ድርጅት አሸናፊነቱ ከተገለፀለት ከ7 ተከታታይ የስራ ቀናት በኋላ ከ8ኛ ቀን ጀምሮ በተከታታይ በ8 የስራ ቀናት ውስጥ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ውል መያዝ የሚችል መሆን አለበት፣
7. ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ በመሙላትና በማሸግ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ድረስ በመቅረብ ጋዜጣው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከተከታታይ 15 ቀናት በኋላ በ16 ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡59 ድረስ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ሲኖርባቸው ጨረታው በዚሁ እለት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 4፡30 ላይ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ውስጥ ይከፈታል፤ ነገር ግን የጨረታ መዝጊያ እና መክፈቻ ቀኑ የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል ፡፡

ሆኖም ተጫራቾች በጨረታው ላይ መገኘት ካልቻሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በጨረታው ላይ ያልተገኙ ተጫራቾች ፖስታን ጨምሮ በእለቱ ይከፈታል፡፡

የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 058 771 66 91/058 178 00 37 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ዩኒቨርሲቲው ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ**



## የጨረታ ማስታወቂያ

ኢትዮ ቴሌኮም የአቧራ ማጥፊያ (Dust Blower) ለማቅረብ ብቁ የሆኑ ተጫራቾችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በጨረታው (ጨረታ ቁጥር 4248930-2) ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ድርጅቶች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ መቶ ብር በመክፈል ከታች በተገለፁት ድረ ገፆች ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡

- የጨረታ ሰነድ ለመግዛት: www.afrotender.com, www.extratenders.com እና www.2merkato.com
- በ ኢትዮ ቴሌኮም አቅራቢዎች ዝርዝር ላይ ለመመዝገብ: “https://erp.ethiotelecom.et/OA_HTML/jsp/pos/suppreg/SupplierRegister.jsp?ouid=0EED8A04B857259C".
- ለማንኛውም ተጨማሪ መረጃ: https://www.ethiotelecom.et/tender/, www.afrotender.com, www.extratenders.com እና www.2merkato.com
- ጨረታው ከሰኔ 17/2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡
- ማንኛውም ተጫራች እስከ ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ከቀኑ 11:00 ሰዓት ድረስ የጨረታ መወዳደሪያ ሰነዱን በኢትዮ ቴሌኮም ዋናው መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 211 ማስገባት ይኖርበታል፡፡ ጨረታው ፍላጎቱ ያላቸው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሐምሌ 12 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በዋናው መ/ቤት ሁለተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 210 ይከፈታል፡፡

**ማስታወሻ**

- ኢትዮ ቴሌኮም የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ጨረታውን በከፊል መወዳደር ይቻላል፡፡

**ኢትዮ ቴሌኮም**